# እግዚአብሔር በገዛ ባህርያቶቹ እራሱን ያስተዋውቃል

ጓደኛየ ዮሴፍ ቦዜ፡ በዚያ በማየቴ፡ ትንሽ ግርምት ነገር ፈጥሮብኛል፣ እና እጁን ልጨብጠው በማለት ዞሬ ትንሽ ጊዜ ወሰድኩኝ።

2 እስኪ አሁን ከእግዚአብሄር ቃል፡ ከእብራውያን፡ 1ኛው ምዕራፍ ላይ እንክፈት። የምሽቱን ርዕሰ ለመሳል ያክል፡ እስኪ ከ1ኛ፣ 2ኛ፣ እና 3ኛ ቁጥሮችን፡ ከፍዬ አነባለሁ።

> ከጥንት ጀምሮ **እግዚአብሔር፡ በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፡**
>
> **በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን፤ ሁሉን ወራሽ፡** ባደረገው **ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት፡**
>
> **እርሱም የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ፣ ሁሉን በስልጣኑ ቃል እየደገፈ፥ ኃጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ... በሰማያት በግርማው ተቀመጠ፤**

3 አሁን ለጸሎት ራሶቻችንን ዝቅ እናድርግ። አሁንም በመለኮታዊ ህልውናው ፊት፡ እሱ እንድያውቅላችሁ የምትፈልጉት የትኛውም ጥያቄ ካላችሁ፡ እባካችሁ እጆቻችሁን ከፍ አድርጉ፡ ይህም ጥያቄአችሁ ነው፡ እግዚአብሄርም...

4 የሰማዩ አባታችን ሆይ፡ አሁን በእምነት፡ በልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ በዙፋንህ ፊት ቀርበናል። "በስሙ የምንጠይቀው ነገር ሁሉ፡ እንደሚሰጠን፡" ይህ፡ የጸና ዋስትና ተሰጥቶናልና። አንተም መሻታችንን እና የጎደለንን ሁሉ ታውቀዋለህ፡ የጎደለንን ነገር ሁሉ እንደምታሟላም ቃል ገብተሃል። ስለዚህ፡ አባት ሆይ፡ አንተው እራስህ እንዳስተማርከን አርገን፡ "መንግስትህ ትምጣ። ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች፡ በምድርም ትሁን" እያልን እንጸልያለን። ይህም ዛሬ ማታ፡ ጥያቄዎቻችን ሁሉ አንተ ልትሰጥ እንደወደድክ፡ እና በልዩ ለእኛ እንደምትሰጠው ጸጋ እንዲሆን ነው። ጌታ ሆይ፡ ቃልህን ቅባው፡ ተናጋሪዎች እና ሰሚዎች ሁሉ ጭምር፣ መንፈሰ ቅዱሰም፡ ዛሬ ማታ በመካከላችን ተገኝቶ፡ የቃሉ ፈጻሚ ይሁን። በስሙ እንጠይቃለንና። አሜን።

ተቀመጡ።

5 ነገ ጠዋት፡ የፉል ጎሰፔል ወንዶች፡ የወንጌል ሰራተኞች ቁርስ እንዳለ፡ አውቄአለሁ። አብዛኛውን ጊዜ፣ አንዳች ምዕራፍ ባለባቸው ቁጥር፣ ቁርሳቸው ላይ የመናገር እድል አገኛለሁ። እስከዚህ ጊዜ ድረስ፡ ተቋም ያልሆነ ድርጅት ይሄ ብቻ ነው፣ እኔ ግን፡ አባል የምሆንለት ብቸኛው—ቡድን፡ የክርስትያን ወንዶች ሰራተኞች ላይ ነው። ስለዚህ አሁን ስለ እነሱ፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ እናገርላቸዋለሁ።

6 አሁን፡ የዛሬ ማታ፡ ሰብሰባችን ለከንቱ እንደማይሆን አምነናል። ዝየ፡ ጎሮሮየም-ተዳክሞ፡ በመጠኑም ብሮንካይት ታምሜ... ነው ወደ እናንተ የመጣሁት፣

7 የመጣሁት በጣም ጥሩ እና ደረቅ ከሆነ ከቱክሰን ነው፣ ወደዚህ ስመጣ ደግሞ እጅግ ተቃራኒው ወደ ሆነው፡ በጣም ጥሩ እና እርጠበታማ ነው። እዚህ ያላችሁ ውሃዎች ሁሉ፡ ወደ እኛ አካባቢ ብትልኩልን፡ እናመሰግናችሁ ነበርን። በርግጥ ግን፡ ይሄን ማድረግ አትችሉም።

8 አንድ ነገር ግን እላችኋለሁ፡ አንድ ምሳሌአዊ አነጋገር አለች ወደዚያ። አሪዞና ውስጥ የሚገኙ የኛ—የኛ—ነገሮቻችን ሁሉ፡ ዛፎቻችን ሁሉ፣ ቅርንጫፍ ብቻ ናቸው። ሁሉ ቅርንጫፍ አለው። ደረቅ ከመሆኑ የተነሳ ነው። ያንኑ ዛፍ እዚህ ቢበቅል ኖሮ፡ በጣም የሚያምር ውብ ቅጠል ይሆን ነበር። እያችሁ፡ ውሃ የለውም፡ ቅርንጫፍ ብቻ የሚቀረው ለዚህ ነው።

9 ቤተክርስትያንም ያለ ህይወት ውሃ ስትቀር፡ ደረቅ እና እንጨታማ ትሆናለች፡ በምንም ነገር ውስጥ፡ እጅግ ትዋጋለች ትደርቃለች። የህይወት ውሃ በሚፈስበት ግን፣ ቅጠሎችን ይዘረጋል ለሰላሳ፡ የጎመራ የጣፈጠ፡ ቅዱስ እና በእግዚአብሔር ፊት ያማረ ያደርገዋል። ስለዚህ ዛሬ፡ እኛም የደረቁ እንዳንሆን፡ እግዚአብሄር ውሃውን ያጠጣን፡ እኛም ዝርግፍ ቅጠል ሆነን ግትሮች ሰዎች ከዛፋችን ጥላ ስር ተቀምጠው ለነፍሶቻቸው እረፍት የሚያገኙብን እንሁን።

10 የዛሬውን ርዕሰ ጉዳይ ወሰጄ፡ ጌታ ከፈቀደ፣ ይሄን ማይክራፎን፡ ድምጼ ከመቀነሱ የተነሣ የተቻለኝን ያህል ለማስጠጋት እየጎተትኩት ነው። እዚህ ዕብራውያን 1:1 ከተነበበው፣ ይሄን ማድረግ ፈልጌአለሁ፡ ይሄን ርዕሰ መውሰድ እፈልጋለሁ: **እግዚአብሔር በገዛ ባህርያቶቹ እራሱን ያሰተዋውቃል።** እንደገና ልበለው፡ የድምጽ ቅንጅቱ መልካም እንዳልሆነ ስለገባኝ ነው። እግዚአብሔር በገዛ ባህርያቶቹ እራሱን ያሰተዋውቃል።

11 አሁን፡ በአብዛኛው ብዙ ነገር የሚታወቀው ባህርዩው ነው። እንድጠቅሳቸው የምፈልጋቸው፡ እንደ... ማስታወሻ ጥቂት ቃላት ይዣለሁ። አሁን፡ የማንኛውም ነገር ባህርይ ምንነትን ያሰረዳል።

12 አሁን፡ እንደ ሌላ ተፈጥሮ ሁሉ፡ ብዙውን ጊዜ፡ አበቦች፡ በገዛ ባህርያቶቻቸው ይለያሉ። ከአንዱ ዝርያ ወደ ሌላው፡ እርስ በርስ ከተቀራረቡ፣ የዚያ አበባ ባህሪ ምን አበባ እንደሆነ ይለያል። እና በዱር አራዊት ውስጥም፡ ብዙ ጊዜ...

13 እኔ—እራሴ አድናለሁ። እና የምታድኑትን እንስሳ ባህርይ ማወቅ ግድ ይላችኋል፣ ካልሆነ ግን አንዳንዴ በትክክል ልትሸወዱ ትችላላችሁ። ለምሳሌ፣ ልክ በብሪቲሽ ኮሎምቢያ ውስጥ እንደሚገኙ ሰቶን ሺፖች። ይሄን ያለፈውን ክረምት በዩኮን አካባቢ ነበርኩና፡ አሁን እዚህ ካሉ ወንድሞች መካከል ሁለት አብረውኝ ነበሩ፡ እና አደን ላይ ነበርን።

14 ልዩነቱን ካላወቃችሁ በስተቀር፡ የበግን ወይም አጋዘን ኮቴ ስትከተሉ፡ ጎበዝ አዳኝ ካልሆናችሁ በቀር ልዩነቱ ይሄ ነው ማለት አትችሉም። ምክንያቱ፡ ተመሳሳይ ኮቴ አላቸው፡ ሲርጡ ሁለቱም ይዘላሉ። ሌላም አንዱ ጭንቅላቱ ደበቅ አርጎ፡ ከርቀት ተመልከቱት፡ በፍጹም፡ ልዩነቱን ይሄ ነው ብላችሁ— አታውቁትም። ወደ ከኋላቸው አካባቢ፡ ተመሳሳይ መጠን አላቸው፡ ልክ እንደ

አጋዘን፡ ነጭ ነው። ይሄ ነው ለማለት እጅግ ይከብዳል። ቀንዱ ግን ማንነቱን ያሳያል፡ በቀንዶቹ። በጉ ጥምዝምዝ ቀንድ አለው፡ አጋዘኑ ደግሞ ወጣ ወጣ ያሉ ነገሮች አሉት። ሌላ ደግሞ፡ አጋዘን እራሱን ለመመገብ፡ ያን ያህል ከፍታ ላይ አይወጣም።

15 ሌላም፡ በተጨማሪ የፍየል፡ አካሄድ፡ የፍየል ባህርይ እና፣ የበግ አለ፡ የሁለቱ ልዩነት ለይታችሁ ማወቅ አለባችሁ፣ ምክንያቱ ወደ ከፍታ ስትወጡ፡ ሁለቱም ከፍ ባለ ተራራ ውስጥ ስለሚኖሩ ነው። ልዩነቱን መረዳት አለባችሁ። አስተውላችሁ ከሆነ ግን፡ ፍየል—ሲራመድ እራሱን የሚያደናቅፍ፡ ሲሆን፡ በግ ሲራመድ ግን፡ እግሮቹን እንዲ **እንዲህ** ያኖራል። የአካሄዱ ባህሪ ዱካውን ይሰራል። ጨዋታ፡ በሚከውነው ስራ እና በአከናወን ሁኔታው፡ በውጤቱ እና በተለያየ ነገሩ፡ ትለዩታላችሁ። በገዛ ባህርይው እራሱን ያሳውቃል። ከዛ በኋላ ወደ ሌላው አልፋችሁ፡ ምን ምን እንደሚከውን ታያላችሁ፡ እንደየ አካሄዱ ይህ ነው ማለት ትችላላችሁ። በየእንስሳው የተለያየ ባህርይ ይህ ይሄ ነው ማለት ይቻላል።

16 የሎሃመር እዚህ ይኑር አይኑር፡ እንጃ እንጂ፡ አስተውላችሁ ታውቃላችሁ፡ በርግጥ፡ ትክክለኛ ሰሙ ፍሊከር ይባላል፡ እና ከጄ በርድ ጋር። ጄ በርድ የተባለው ወፍ መጠኑ የየሎሃመር ዓይነት ነው። እና እነዚህ ሁለቱ ሲበሩ ብታዩአቸው፡ ሁለቱ አንድ አይነት ወፍ ይመስላሉ። ቀለማቸውን ካላያችሁ፡ ብቻ ተመልከቷቸው፡ የሎሃመር የቱ እንደሆነ መናገር ትችላላችሁ። ጄ በርድ፡ ይብዛም ይነስ፡ እንደ ንብ ይበራል። የሎሃመር ግን፡ ክንፎቹን ያንዣብባል፡ ክንፎቹን ሲያንዣብብ፡ ወደ ታች ወደ ላይ፡ እንደገናም ወደላይ ወደ ታች ይወርዳል። አያችሁ፡ ልክ **እንደዚህ** እራሱን ያሰራል፣ ስለዚህ የየሎሃመርን አበራረር አይታችሁ፡ ባህሪውን ማወቅ ትችላላችሁ።

17 ጅግራ—ሲወጣ፡ ወደ ላይ አወጣጡ ካስተዋላችሁት። ከዛ በኋላ ጅግራ፡ ምናልባትም—ሰናይፐን፡ ውሃ ባቆረበት አካባቢ ደግሞ ተመልከቱ። አዳኞች ይሄን ታውቃላችሁ። ዊልሰንስ ሰናይፕ እና ጃክሰናይፕ፡ በአወጣጣቸው እና አበራረራቸው ይታወቃሉ። ምን አይነት የወፍ ዝርያ መሆናቸው፡ በአበራረራቸው ባህርይ ይታወቃሉ። ስለዚህ፡ ከሰማችኋቸው፡ ምንነታቸውን ማወቅ ትችላላችሁ፡ በእነሳስ አይነቱ፡ በአበራረሩ ባህርያት፡ ማን ነው ይታወቃል።

18 ልክ እንደ ወንድ እና እንደ ሴት። ሁለቱም ሰዎች ናቸው፡ ነገር ግን ሴት ከወንድ የተለየ ባህርይ አላት። ከተወሰነ ጊዜ በፊት፡ ስለ ሰለሞን እና ስለ ንግስቲቱ፡ እዚህ እያነበብኩ ነበር። ትንሿ ሰብከቴን፡ እዚህ በእናንተ ዘንድ ፈጽሜ ሰብኬው አላውቅም፡ የደቡቧ ንግስት፡ ሰሎሞንን ለማየት መጥታ፡ ያንን ሀሳብን የሚያነብበት ጸጋ ማየቷ። በቅርብ ጊዜ፡ ስለሱ እያነበብኩ ነበር፡ እና እነሱ ሲናገሩ፡ “ለሰለሞን ከቀረቡለት እንቆቅልሾች አንዱ፡ ይቺ ንግስት፡ ሴት ወሰዳ፡ ሴቶችን ወሰዳ፡ የወንድን ልብስ አለበሰቻቸው።”

19 እና፡ በዚያ ጊዜ እንግዳ ነገር ነው፡ ለዚህ ዘመን ግን፡ በርግጠኝነት-ወቅ-ታዊ ነው። እናንተ—እንደምታውቁትም ስህተት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ሴቶች እንዲህ ማድረግ የለባቸውም ይላል። “ሴት የወንድን ልብስ ብትለብስ ነውር ነው።” የማይቀየረው አምላክ ይህን ተናግሯል፡ ስለዚህ እውነት ነው።

20 ሰለሞንም እንዳያቸው፡ ወድያው ያደረገው ስንመለከት፡ እንዲራመዱ ወይም የሆነ ነገር አደረጋቸውና፡ ወዲያውኑ "ሴቶች ናቸው" አለ። አያችሁ፡ በሴቲቱ መገለጫዎች ምክንያት፡ እራሷን ባከናወነችበት መንገድ፡ ሴት እንጂ ወንድ አለመሆኗ ማወቅ ችሏል።

21 ሌላውም ሁሉ በብዛት፡ በገዛ መገለጫዎቹ ነው። ብዙዎች ግራኝ-እጅ፡ እና ቀኝ-እጅ እንደሆኑ ሁሉ። ሰዎች ነገሮችን የሚከውኑበት ባህርይ ይገልጻቸዋል። እራሳቸውን በሚያሳዩት ባህርይ ምክንያት፡ ይህ ሰው ቀኝ- ወይም ግራኝ-ነው ለማለት ትችላላችሁ፣ አዘውትረው በግራ እጅ ወይ በቀኝ እጅ በሚሰሩት ስራቸው ይለያሉ።

ኢየሱስ፡ እንዲህ አይነት ነገር እንደነበረው፡ አስታውሱ...

22 ሁለት እጆችም እጅግ ተቀራራቢ ናቸው... አንድ አይነት ናቸው። ሁለቱም ተመሳሳይ የአውራጣት አሻራ፣ የጣት አሻራ፣ አምስት ጣቶች፣ ትንሿ፣ ጠቋሚ ጣት፣ ወዘተ አላቸው። ልክ እንደ ቀኝ እጅ ግራ እጅም ተመሳሳይ አይነት ጣቶች፣ እንዲሁም፡ ተመሳሳይ መጠን ያለው፡ አንድ አይነት እጅ ነው። በመካከላቸው ያለው ልዩነት፡ አንደኛው ግራ ሲሆን፡ ሌላኛው ቀኝ መሆኑ ብቻ ነው። አለ ይሚባል ብቸኛው ልዩነት ይህ ብቻ ነው። አንደኛው ግራ ነው፡ ሌላኛው ቀኝ ነው።

23 ስለዚህ በዚያም፣ ኢየሱስ እንዳለው... ምናልባት እዚህ ላይ አንድ ነጥብ ላስቀምጥ። ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል 24፡ ላይ፡ እንዳለው "በመጨረሻ ዘመን የመንፈስ ባህርያት የመመሳሰል አዝማሚያ ይኖራል፣ የሚቻል ቢሆን ኖሮ የተመረጡትን እንኳን እስኪያስት ድረስ ብሏል።" አያችሁ፡ ልክ እንደ...

24 እጆቻችሁን አውጡና ከፍ አድርጓቸው። እስኪ እዩትና፡ አንደኛው ከሌላኛው ጋር መመሳሰሉን ካላስተዋልችሁ ተመልከቱ፣ በሁሉ ይመሳሰላል፡ ነገር ግን አንደኛው ግራ ነው ሌላኛው ቀኝ።

25 በመጨረሻ ዘመን ያለው መንፈስም ልክ እንዲህ ነው። በብዙ መንገድ አንድ ናቸው፡ ነገር ግን ሁለቱ የሚታወቁበት የየራሳቸው ባህርያት አላቸው። አንደኛው ትክክለኛ ነው፡ ሌላኛው ግን ስህተት ነው፡ የሚታወቀው ግን በባህርዩው ነው።

26 የእግዚአብሄር መንፈስ በባህርይው ሊታወቅ ይችላል። አያችሁ? የእግዚአብሄር መንፈስ፣ እና የቤተ ክርስትያን መንፈስ። የቤተ ክርስትያን መንፈስ አለ፡ እንዲሁም ፈጽሞ እንደ ቤተ ክርስትያን መንፈስ ያልሆነ፡ የእግዚአብሄር መንፈስም አለ።

የኃይማኖት መንፈስ አለ።

27 አገራዊ መንፈስ አለ። የአገር መንፈስ አለ። በሄድኩበት፡ ወይም በሄዳችሁበት፡ አገር ሁሉ፡ የተለየ መንፈስ ታገኛላችሁ። ፊንላንድ ሄጃለሁ፡ ህዝቡ በጣም ደስ ይላል፡ ነገር ግን ፊኒሻዊ መንፈስ ነበር። ጀርመንም ሄጃለሁ፡ ጀርመናዊ መንፈስ አለ።

28 ብዙም አልቆየም፡ የዛሬ ሁለት ዓመት ነው፡ ኑሯችን በኢንዲያና በነበረ ጊዜ፡ እኔና ሚስቴ፡ ወደ አንድ ሱፐርማርኬት እየሄድን ነበር። ቤት ገና መድረሴ ነበርና። አንዳንድ አስቤዛዎች ማድረግ ነበረብን። እና በመንገድ ላይ ሳለሁ፡ አብረን... በጋ ነው፡ ላታምኑት ትችላላችሁ፡ ነገር ግን ቀሚስ የለበሰች ሴት አጋጠመችን።

ለየት ያለ ነው፡ እኔ... ገርሞኛል። እኔ—እኔም “እዚያ ጋር ተመልከቺ፡ በጣም ይገርማል፡ ያቺ ሴት ቀሚስ ለብሳለች” አልኳት። ሌሎቹ ያልተገባ... የሴት ልብስ ያይደለ ልብስ ለብሰው ነበር። እና—እሷም አለችኝ... እንዲህ አልኳት፦ “እንግዲህ፡ የአሜሪካ መንፈስ፡ አየሽ፡ የአሜሪካ መንፈስ ይሄ ነው።”

29 አሁን፡ የአሜሪካ መንፈስ... ክርስትያን አገር ትባላለች፡ የአገሪቱ መንፈስ ግን ክርስትያን አይደለም። የክርስትያን አገር ልትባል ትችላለች፡ ነገር ግን በመገለጫዎቿ፡ ከክርስትና በሚልዮን ማይሎች ርቃለች። ስለዚህ፡ ይህች ሴት፡ እንዲህ አልኩ...

እንዲህ አለች፦ “እሺ፡ እኛ አሜሪካውያን አይደለንም’ዴ? ”

30 አለች፡ እኔም፦ “አይደለንም። እዚህ እንኖራለን። አገራችን ነው። እኛ—እኛ—እንቆይባታለን። እንወዳታለን። በአለም ከሚገኙ ሁሉ ይልቅ የበለጠች አገር ናት። ቢሆንም፡ አሜሪካውያን ግን፡ አይደለንም።” “ትውልዳችን ከላይ ነው። መንፈስ ቅዱስ ወርዷል፡ የሌላ መንግስት ዜጎች ነን። ከዚህ አለም ግን አይደለም፡” አልኳት። እኔም፦ “እህቶቻችን ቀሚስ የሚለብሱት፡ ረዣጅም ጸጉር የሚኖራቸው፡ ሜክ-አፕ የማይጠቀሙት ለዚህ ነው አልኳት። አየሽ፡ ባህርያቶቻቸው ከላይ ለሆነው ጌታ ‘ቅድስና መሆናቸውን፡’ የሚያስረዳ ነው።”

31 ስለዚህ፡ መንግስትን የምንጠብቅ ነን። የእርሱ የሆኑትን ወደ መንግስቱ ለመውሰድ የሚመጣ ንጉስን በመጠባበቅ ነን። እነሱም በገዛ—ባህርያቸው ይታወቃሉ፣ ይህም ሀብታቸው ከላይ ከክብር እንጂ። ከዚህ ምድር፡ ወይም ከዚህች አገር አለመሆኑ ነው። በትክክል ተለይተው ይታወቃሉ። ስለዚህም፡ “ፈጣሪዋ እና ሠሪዋ እምላክ የሆነላትን ከተማ ይጠብቃሉ።”

32 በጥሩ ድምጽ ለእናንተ የምሰብክባት አንዲት ምሽት ባገኝ ተመኘሁ። ይሁን እንጂ—ከዚያ ወጥቻለሁ። አሁን፡ በገዛ ባህርይው ይታወቃል።

33 እዚህ ላይ እስራኤል ወደ ተስፋይቱ ምድር ሲገቡ፡ ጥሩ ምሳሌ እናገኛለን። እግዚአብሄር እንደተስፋ ቃሉ ጠራቸው። እሱም አብራሃምን ተናግሮ፡ ዘርህ በዚህች እንግዳ ምድር ላይ... ለአራት መቶ አመታት፡ እንዲህ እና እንዲያ ይሆናል፡ ከዚያ በኋላ ግን በታላቅ ክንዱ ያወጣቸዋል፣ ከዚያም፡ ማር እና ወተት ወደምታፈሰው፡ ወደተስፋይቱ ምድር፡ ይወጣሉ ብሎታል። የተሰፋው ቃል ዘመን በቀረበ ግዜም፡ ዮሴፍ በመካከላቸው የሰራውን ታላቅ አገልግሎት—የማያውቅ ፎርኦን ተነሳ።

34 እግዚአብሔርም፡ ሙሴ የተባለውን፡ ይህን ነቢይ አስነሣው። ሰውዬውም የግብፃውያንን ጥበብ ሁሉ ተማረ። የግብፃውያንን ጥበብ ማስተማር ይችል ነበርና፣ ታላቅ፡ ብልህ፡ ምሁር ሰው እንደነበር ጥርጥር የለውም። ነጻ ለማውጣት—በትክክል የሚመጥን ሰው ይመስላል።

35 ነገር ግን፡ አያችሁ፡ እኛ የምናስበው ነጻ ማውጣትና፡ እግዚአብሄር የሚያስበው ነጻ ማውጣት፡ ይለያያል።

36 አሁን ይህ ሰው ከዚህ ሁሉ ሥነ ምግባሩ ጋር ተመልከቱት። የእስራኤልን ልጆች ለማዳን መወለዱን ያውቃል። ቢሆንም፡ ከዚህ ሁሉ ትምህርቱ ጋር፡ እውቀቱ ይህ ብቻ ነበር፡ ሰራውን ይሰራለት ዘንድ በእግዚአብሄር የተጠራ መሆኑንን አውቆ፡ ብዙ ነገር ነበረው... ባችለር ኦፍ አርት፡ ፒኤች.ዲ.፣ እና

ኤልኤል.ዲ.፣ ወዘተረፈ ነበረው። በዚህም እስራኤልን ነጻ ሊያወጣ ተነሳ፡ ፈጽሞም ወደቀ።

37 አሁን አስተውሉ፡ ፎርኦን ለመሆን፡ የግብጽን ዙፋን ለመውረስ መቃረቡ፡ ስለተቃረበ፣ ፎርኦን ከሆነ በኋላ የእስራኤል ልጆችን ነጻ ማውጣት እንደሚችል መሰሎታል፣ ምክንያቱ ዙፋን ላይ ለመውጣት—አልጋ ወራሽ ነበር። እያችሁ ግን፡ ይህን በማድረግ፡ ህዝቡን፡ በዚህ መንገድ ነጻ በማውጣት፡ የእግዚአብሄር ባህርይ የሚያሳውቅ አይሆንም።

38 እሱ እራሱ ነጻ አወጣቸዋለሁ። "በብርቱ ክንድ ነጻ አወጣቸዋለሁ" ብሏልና፣ እግዚአብሔር በጽኑ እጅ ነው እንጂ፡ በሙሴ ብርቱ ሠራዊት አይደለም።

39 ይህ ነቢይ ሸሽቶ ለአርባ ዓመታት ያህል በምድረ በዳ እንደኖረ እውቀናል። ፎርኦን እውቀትን እንዲከምርበት አርባ ዓመታት ቆፈረ፡ እግዚአብሄርም ያንን ለማራገፍ አርባ ዓመታት ቆፈረ። ስለዚህ እንዳየነው፡ አንድ ቀን፡ በምድረበዳው ማዶ፡ በሚነድ ቁጥቋጦ፡ ጌታ እግዚአብሄር በቁጥቋጦ ላይ እንደሚነድ የእሳት አምድ ተገናኘው። የረገጠው ቦታ የተቀደሰ ነውና፡ ጫማውን፡ እንዲያወልቅ ታዘዘ። አሁን ይህ መልካም፣ ዘመናዊ፣ ምሁር የሆነ ሰው እዩት፣ ከእግዚአብሄር ጋር ከተገናኘ በኋላ የተቀየረ ባህርዩው ተመልከቱ። እጅግ የሚገርም...

40 አንዳንዴ እግዚአብሄር፡ በሰጋ ለሚያሰብ፡ እንዲህ ቀለል ባለ እና ሞኝ በሆነ መንገድ ይሰራል። የእግዚአብሄርን ፈቃድ ለማድረግ፡ የግብጽን ሰራዊት እና ሌላው ሁሉ ከእርሱ ጋር ሆኖለት ሙሉ ለሙሉ የወደቀውን ሰውየ አስተውሉት፣ በአርባ ዓመቱ፡ ከመዓርጉና፡ ከዚህ ሁሉ እውቀቱ ጋር ወደቀ። በነጋታው፡ በሰማንያ ዓመቱ፡ ሚስቱን በበቅሎው ላይ ታናሹ ልጅ ዳሌዋ ላይ አሰይዞ፡ ይሄው፡ ዱላውን በእጁ ጨብጦ፡ ግብጽን ለማሸነፍ፡ ጉዞውን ጀመረ። ስለሚገርም ትዕይንት ትናገራላችሁ! ያ ግን ቃሉን የሚያምን ሰው ስለተገኘ፡ የእግዚአብሄርን ባህርይ እያሳየ ነበር። ይሄው ነው። የሚገርመው ደግሞ፡ ያኔ፡ በሰራዊት ያልቻለውን፡ አሁን አንድ-ሰው ብቻውን ግብጽን ለመውረር ሲነሣ መገመት ትችላላችሁ ወይ? ታድያ ምንድነው? ባህርያቶቹ፡ ሰልቶቹ ተቀየሩለት። "እኔ እኔ ነኝ፡" የሆነውን የጌታን ሰም ይዞ ሄደ። የሚገርመው ደግሞ፡ ማሸነፉ ነው። በጌታ ስልጣን ስለወጣ፡ አሸነፈ።

41 እስራኤልን ወደ ተስፋይቱ ምድር መርቶ ለማውጣት፡ መንገድ ላይ ሳለ፡ ከወንድሙ፣ ከሞዓብ ጋር ተገናኘ፡ ድርጅታዊ ወንድሙ። አሁን፡ ሞዓብ፡ በምንም መልኩ፡ እምነት አልባ አልነበረም። የሎጥ ሴት ልጅ ልጅ ነበርና። ከሁለቱ ልጆቹ አንዷ—ሞዓብን ወልዳለታለች።

42 አሁን፡ እዚያ ጋር፡ እነዚህን ሁለት ወገኖች፡ በንጽጽር እንድታስተውሏቸው እፈልጋለሁ። እዚህ ጋር በግብጽ፡ አነሰተኛው፡ የተበታተነ፡ የሚኖርበት አገር የሌለው፡ መኳንንት እና ንጉሰ፡ ወይም ምንም የሌለው፡ ወይም በመካከላቸው ከበርቴዎች የሌላቸው፡ ወደ ተስፋይቱ ምድር የሚጓዝ ህዝብ ብቻ ናቸው። እዚህ ጋር ደግሞ በተስፋው ምድር መንገድ ላይ ስለነበረች። በሞዓብ ምድር ማለፍ አለበት።

43 እንዲሁም፡ ሞዓብ፡ በያህዌ የሚያምኑ አማኞች ነበሩ፡ ነብዩም ነበራቸው። እስራኤልም ነብዩ ነበራቸው። ሁለቱ ነብዩ ነበራቸው።

44 ስለዚህ አሁን አስተውሉ፡ እዚህ ላይ ሲደርሱ ይህ ከተደራጀች አገር የሆነው ነብዪ ሌላውን ህዝብ ለመርገም ወረደ፡ ምክንያቱ ተጎታች ስለነበረ ነው፡ የሚጸኑበት ስፍራ የላቸውም። ስለዚ ወረዱ።

እና ሁለቱ ነብያቶች ተመልከቷቸው: መሰረታዊ በሚባሉ ነገሮች ከተነጋገርን፡ ሁለቱም ፍጹም ትክክል ነበሩ። ምክንያቱ፡ አስተውሉ፡ ጳጳሱ፡ በልዓም፡ "ሰባት መሰውያዎችን፡ አሁን ሰራልኝ፡" ብሎታል።

45 ሰባት ማለት የሰባቱ አብያተ ክርስትያናት፣ እና ሰባቱ የፍጠረት ቀናት፣ ወዘተ፣ የሚወክል የእግዚአብሄር የሙላት ቁጥር ነው። አሁን፡ ሰባትን አስተውሉ፡ እግዚአብሔር በሰባት ሙሉ ይሆናል።

46 "ሰባት መሰውያዎች፡ በእያንዳንዱ መሰውያም—አንዳንድ በሬዎችን አኑር።" ይህ ማለት በእስራኤል ማደርያ እንደነበረ አይነት መሰውያ ነው። እዚህ እንደነበራቸው፡ አንድ አይነት መሰውያ ይዘው፡ አንድ አይነት መሰዋዕት ጋር ወደ እስራኤል ወረዱ፡ በሬ እና በሬ፣ ነብዪ እና ነብዪ። ሁለት ወገኖች፡ በንጽጽር።

47 ይህ ማለት አሁን እኛ የምንኖርበትን ዘመን ትክክለኛ ምሳሌ፡ ጊዜ ካለን የምናየው ይሆናል። አስተውሉ፡ እግዚአብሄር ምናልባት በንጽጽር እንዲገባን፡ ይህን ነገር በምሳሌ ሰራው።

48 አሁንም፡ በልዓም፡ በእያንዳንዷ መሰውያ ላይ በግ ይጠይቃል። ይህም በሚመጣው መሲህ ያለውን እምነት ይናገራል። በእስራኤል ዘንድ የነበረው መሰዋዕት፡ ይሄው እራሱ ጠቦት፡ ተባት በግ ነበር። በሞዓብ... በነበረው፡ በእስራኤል ማደርያም እንዲሁ ነበር። ያንን... መሰረታዊነታቸው፡ ሁለቱም ትክክል ነበሩ፡ ይሁን እንጂ፡ አስተውሉ፡ መሰረታዊ ትምህርት ላይ ነው።

49 በእስራኤል ማደርያ ዘንድ የነበረው አንደኛው ነብዪ ግን የእግዚአብሄር ባህርያት እና የእግዚአብሄር ቃል ነበረው። ለዚያ ዘመን ከተሰጠው የእግዚአብሄር ኪዳን ጋር ጸና፡ ምክንያቱ ወደ ተሰፋይቱ ምድር ለመሄድ ጉዞ ላይ ነበርና። አያችሁ?

50 አሁን፡ መሰረታዊ በሚባል ነገር ላይ፡ በልዓምም፡ ባላቅም ልክ እንደ ሙሴ ሊታወቁ ይችላሉ።

51 አያችሁ፡ ሙሴ፡ ግን፡ የእግዚአብሄር ትክክለኛ ነብዪ ሆኖ፡ መሰረታዊ የሚባሉ ክፍሎች ብቻ ሳይሆኑ፡ የእግዚአብሄር መታወቂያም ጭምር ነበረው። አያችሁ፡ ለኖህ ዘመን ሳይሆን፡ ያኔ ለነበረ ትውልድ፡ ለዚያች ዘመን ለተሰጠው ኪዳን፡ በሰራው ዘርፍ ላይ ነበረ። "ማር እና ወተት ወደምታፈስው ምድር አገባችኋለሁ።" በጉዞ ላይ ነበሩ፡ እስራኤላውያንም፡ በዚያ ዘመን ለነበረ መልዕክት፡ ከነብያቸው ከሙሴ ጋር የተለዩ ነበር። የእግዚአብሄር ባህርያት በሙሴ ላይ ታወቀ። የእሳቱ አምድ ይከተለው ነበር። በተጨማሪም ማስተሰረያው በተግባር ከእርሱ ጋር ነበር፡ ስለሱ ይናገር ነበር ሳይሆን፡ በተግባር ነበረው። ምን ይሆናል ሳይሆን፡ አሁን ምን ሆነ!

52 ስለ ሕዝቡ ደዌ እና በሽታ የተሰቀለ ከነሐስ የተሰራ እባብ እንደነበረውም፡ አስታውሱ፡ ስለዚህ ሙሴ መለኮታዊ ፈውሰም ያደርግ ነበር። እግዚአብሔር በሰፈሩ ውስጥ እንዳለ የሚያመለክት የናሱን እባብ ማስተሰረያ ነበረው። ሕዝቡም የናሱን እባብ አይተው ይፈወሱ ነበር።

53 እንዲሁም የሚከተለው የተመታ አለት ነበረው። ይህም እግዚአብሄርን የሚያስተዋውቅ ነበር፡ በመካከላቸው የሕይወትን ውሃ፡ የዘለአለም ህይወት እንዲኖራቸው እንጂ እንዳይጠፉ፡ ደስታ እና መዳን ነበራቸው። ይህ ጥላ ነበር… በምድረበዳው የተመታው ዓለት የክርስቶስ መመታት የሚያስረዳ ነው።

54 ስለዚህ፡ በቃል ኪዳን መስመር ይጓዙ ነበር። ይህም የእግዚአብሄርን ባህርያት ለማሳየት፡ ሌላ መለያ ነበር። ይሄ ሌላኛው ምንም ያህል በቃሉ ላይ መሰረታዊነት ያለው ቢሆንም፡ መሰረታዊነት ነበረው፡ በተጨማሪም መታወቅያ፡ እና የእግዚአብሄር ባህርይ በአንድነት በመካከላቸው ነበረ። አምላክ እራሱን አስተዋወቀ። ሁለት ነብያቶች፡ ሁለቱ ነበዪ ናቸው፡ እንዲሁም ሁለቱ መሰረታውያን፡ ግን ባህርይው ግን እግዚአብሄር በሙሴ ላይ አሳየ፡ ምክንያቱ የእግዚአብሄር ባህርያት ከእሱ ነበር።

55 አሁን፡ እንደገና፡ እግዚአብሄር መለኮት ስለሆነ፡ ባህርያቱም ዘወትር መለኮታዊ ነው። እግዚአብሄር መለኮታዊ ነው። ሁሌም ቢሆን፡ በየዘመኑ ላለ ዘመናዊ አስተሳሰብ፡ ያልተለመደ አካሄድ ነው። እናንተም ታውቃላችሁ። እግዚአብሄር ሁሌም ስርዓቶችን፡ በዘመናት ሁሉ ያለፉትን የሐይማኖት—ድርጅቶች ሁሉ በታትኖባቸዋል።

56 ስለዚህ በግልም ቢሆን በቡድን በመልዕክት ዙርያ ሰዎች እራሳቸውን አደራጅተው በየተራቸው ያልሞቱ የሉም፡ ፈጽመው ደግመው አልተነሱም። በታሪክም የለም። ሉተራኖች፡ ፕሪስባይተሪያኖች፡ ሜቶዲስቶች፡ ባፕቲስቶች፡ ጴንጤቆስጤዎች፡ እና ሌሎችም፡ ለመደራጀት በሄዱ ግዜ ፈጽመው አልተነሱም።

እግዚአብሔር የሚሰራው ከግለሰቦች ጋር ነው።

57 አስተውሉ፡ ለማሰብ እጅግ አስቸጋሪ ነው። አያችሁ፡ በልምድ እንወስዳለን፡ **እንዲህ** ማመን ግን ይጠበቅብናል። ከዚያ በኋላ እግዚአብሄር የገባልንን ቃል ይዞ ይመጣል፡ እራሱንም በዚያች ቃል ያስተዋውቃል። **ይሄኛው** ቡድን ግን ስለማያምንበት፡ ወደ እንደዚህ አይጠጋም። አያችሁ፡ እራሳቸውን ከእሱ ቆርጠው ይለያሉ።

58 እንደ ዮሴፍ፡ የዳዊት ልጅ እና መልካም ሰው ነበር፡ ዮሴፍ የማርያም ባል። ያለጥርጥር መጽሐፍ ቅዱስን፡ ብራናውን፡ ዘወትር የሚያነብ፡ መልካም ሰው… መሲሕ እንዲመጣ የሚጠባበቅ ሰው፡ ኢሳያስ "ድንግል ትጸንሳለች።" እንዳለው፡ ቅዱስ ቃል ይሆናል ያለውን ነገር እንደሚሆን የሚያውቅ ሰው ነው።

59 እንግዲህ፡ አሁን፡ እሱ ከማርያም፡ ከወጣቷ እጮኛው ጋር ይሄዳል፡ ምናልባት እሷ የአስራ ሰምንት አመት፡ እሱ ምናልባት በእድሜ ይበልጣታል። ሁለቱ ሊጋቡ ታጭተው ሳሉ ግን፡ ጸንሳ ተገኘች። አሁን ዮሴፍ ይሄን ለመቀበል ከአቅሙ በላይ ሆኖበታል። ማርያም የገብርኤል ጉብኝት ያለጥርጥር ሳትነግረው አትቀርምና። እንደ'ሱ ባህርይ፡ ሰናስተውል ግን፡ ተጠራጥሯታል።

60 እሷ ከመጋብቻቸው በፊት ጸንሳ ተገኝታለች። እና፡ በመጽሐፍ ቅዱስ፡ ቅጣቷ፡ በድንጋይ ተወግሮ መሞት ነው። ሳታገባ ጸንሳ የምትገኝ ሴት፡ በድንጋይ ትወገራለች። በእስራኤል ዘንድ ዘሟዊነት አልነበረም። ዋጋውን ያገኛል። ይሄን የሚነግረን፡ በዘዳግም፡ እናገኛለን።

61 ማርያም ስለፈጸመችው ተግባር፡ ዮሴፍን እንደ ጋሻ መጠቀም እንደፈለገች፡ መስሎ እናገኘዋለን። ምክንያቱ፡ ገና ሳይጋቡ ጸንሳ ከተገኘች፡ እንግዲያው መወገር ነበረባት፡ ስለዚህ ለእሷ እንደ ጋሻ የሚቆምላት አንድ ሰው ያስፈልጋት ነበር። እና በአጠቃላይ፡ ይህ ሁሉ ትዕይንት፡ ይሄን ለማድረግ የምትሞክር አስመስለባት።

62 ዮሴፍ ግን ሰትነግረው፡ ትልልቅ አይኖቿን እያየ፦ "ዮሴፍየ፡ ገብርኤል እንደነገረኝ፡ 'መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይጸልልሻል፡ስለዚህ ደግሞ በአንቺ—በአንቺ የሚጸነሰው የመንፈስ ቅዱስ ነው። ከእግዚአብሄር ነው። መጠርያውም፡ "የእግዚአብሄር ልጅ" ተብሎ ይጠራል።'" ዮሴፍም፡ በርግጥ፡ ነገሩን—አምኖ—መቀበል ፈልጓል፡ ግን በጣም ያልተለመደ ሆነበት። ከዚህ ቀደም አጋጥሞ አያውቅም።

63 ዛሬም ቢሆን ያው ነው። ብቻ ይሄን ነገር... ህዝቡ የነገሮችን ሁሉ አለመለመድ ማሳየት የምችልበት መላ በኖረኝ፡ በቃሉ የታወቀ ከሆነ፡ እሱነቱን ባህርዩው ራሱ ያረጋግጠዋል። እግዚአብሄር በሰራ ላይ ነውና።

64 ዮሴፍ ይሄን ማወቅ ነበረበት። "ድንግል እንደምትጸንስ፡" ይሄን ማወቅ ነበረበት። እሱ በዚህ ጉዳይ ጻድቅ ነበር። ሊያባርራት አልወደደም፡ በምስጢር ግን፡ ማድረግ ያለበትን—ያሰብ ነበር።

65 የጌታም መልአክ በህልም ተገለጠለት። በህልም ለምን ተገለጠ ብላችሁ አስባችሁ ታውቃላችሁ? በነዚያ ዘመን ነብያት አልነበሩም። ህልሞቻቸው ትርጓሜ የማይሹ፡ ቀላል ናቸው። እንዲህ አለው፦ "የዳዊት ልጅ፡ ዮሴፍ ሆይ፡ ሚስትህ ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ፡ በእሷ የተጸነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና።" አያችሁ፡ ወድያው፡ ነገሩ ቦታውን አስያዘ። አያችሁ፡ በሁለተኛው ደረጃ፡ በህልም ወደሱ መጣ። አያችሁ ግን፡ "የምታረግዘዋ ድንግል ይህች መሆኗን፡" መመርመር የሚችል ነብዪ፡ በዚያ፡ አልነበረም። አያችሁ? ስለዚህ፡ እሱ ቅን እና ጻዲቅ መልካም ሰው ስለነበረ፡ በዚህ ምክንያት፡ በህልም ተገለጠለት።

66 መልካም ለሆነ ሰው ሁሉ፡ እግዚአብሄር በዚህ መንገድ እንደሚመጣለትና፡ በዚያው ዘመን፡ ሰውየው ለዚያ ዘመን የተጠራ ሰው ከሆነ፡ ሰራዎቹን ሁሉ ለዚያ መልካም ሰው እንደሚያስታውቅ አምናለሁ።

67 አሁን ግን፡ እጅግ ያልተለመደ ስለሆነ፡ ሊቀበሉት አልቻሉም። ነገር ግን፡ ሁሌም ቢሆን፡ ለዘመኑ በተሰጠ የተሰፋ ቃል መሰረት የሚገለጥ ነገር ሁሉ፡ ያልተለመደ ነው።

ምናልባት አሁን አንዳንድ ሰዎች ተነሰተው፡ "አዎን፡ **ይሄ** ያልተለመደ ነው፡ ስለዚህ አምላክ ነው። **ይሄ** ያልተለመደ ነገር ነው፡" የሚሉ ይኖራሉ።

68 ነገር ግን አያችሁ፡ ከቃል ጋር መታወቅ አለበት፡ ቃሉም እግዚአብሄር ነው። አያችሁት? ከዚያ በኋላ የዚያን መለያ ባህርያቶች ማንነቱን ያስታውቃል፡ ምክንያቱ እግዚአብሄር፡ "**እንዲህ** ይሆናል፡" ያለውን ስለተፈጸመ። አያችሁ? የነገሩ ባህርያት የእግዚአብሄር ቃል በተግባር በሚፈጸምበት ባህርያት የሚታወቅ ነው።

69 በመጨረሻው ዘመን መንፈስ ቅዱስን አፈስሳለሁ አለ። አፈሰሰው። የዚህ ነገር ባህርይ፡ ቃሉን የገባ እግዚአብሔር መሆኑን ያስታውቃል። እያችሁ፡ እሱ ሁልጊዜ እራሱን ያሳያል።

70 አሁን፡ ዘወትር፡ ሁሌ፡ ቃሉ በስሕተት ሲባል፡ የሚያርመው፡ ቃል እራሱ ነው። አስተውላችሁ ታውቃላችሁ? ያንን ሳይንሳዊ ዘመን ያረመው፡ በኖህ ዘመን ነበር፡ እግዚአብሄር ከሰማይ ውሃ ሊያወርድ ነበርና። እያችሁ፡ ሁሉም በግብጽ ተደላድለው ወዘተ በነበሩ ጊዜ፡ ያንን ያረመው፡ ሙሴ ነበር፡ የእግዚአብሄር ቃል ሊታወቅ ይገባዋልና። ስለዚህ የቃሉ እውነት ስሕተትን ያርማል።

71 አንድ ነገር ልጠይቃችሁ እስኪ። ምናልባት እዚህ ጋር ትንሽ ዘልቀን እንገባለን። ትምህርት ወይም ስረተ እምነት መሰበክ አይጠበቅብኝም፡ ግን እስኪ አንድ ነገር ልጠይቃችሁ።

72 ኢየሱስ ቃል ነበር። ይሄን እናውቃለን። መጽሐፍ ቅዱስም ይህን ይናገራል። ቅዱስ ዮሃንስ፡ 1ኛው ምዕራፍ፦ "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ቃልም ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ።" አሁንም ድረስ ቃል ነው። እና ሐሳባቸውን ማንበብ በቻለ ጊዜ፡ እሱ ራሱ ቃል መሆኑ ሊያውቁት ይገባቸው ነበር፡ የእግዚአብሄር ቃል ስለሱ ይህን ያደርጋል ብሎታልና። ነብዩ እራሱ ነበር።

73 አሁን አስተውሉ፡ በተውለደ፡ አስራ ሁለት አመት ሲሞላው፡ ወደ ዳስ በዓል ወጣ። ሁሉም ወደ ፋሲካው በዓል ሄደው ነበርና። እና፡ ሲመለሱ፡ የሶስት ቀን ጉዞ ተጓዙ አጠገባቸው ግን አልነበረም፡ ከዘመዶቻቸው በህዝቡ መሀል ይኖራል ብለው፡ አሰበው፡ ተቀብለው፡ ወይም ገምተው ነበርና።

74 ከዚህ ብዙ ክፈለ ጊዜ ማውጣት እንችላለን። ዛሬ ዛሬ እጅግ የተለመደ ነው! አሁን እናንተ ሜቶዲስት፣ ባፕቲስት፣ ፕሪስባይቴሪያን፣ ሉተራን፣ ካቶሊክ፣ እያችሁ፡ የትኞቹ የሆናችሁ፡ እናንተም ያንኑ እየደገማችሁ ናችሁ። ዌስሊ ታላቅ ሪቫይቫል ስለነበረው ብቻ ትቀበሉታላችሁ፡ ሉተር ታላቅ ሪቫይቫል ስለነበረው፡ ወይም ጴንጤቆስጤ ታላቅ ሪቫይቫል ስለነበራቸው፡ እንደው፡ እንዳንዱ በህዝቡ መካከል እንኳን ሳይኖር፡ አለ ብለን እናሰበዋለን።

75 ፍለጋውን ሄዱ። የት አገኙት? በተውበት ቦታ፡ በኢየሩሳሌም። ባገኙትስ ጊዜ፡ ምን እያደረገ ነበር? ታዳጊ የአስራ ሁለት ዓመት፡ ምናልባት እናቱ ከምትነግረው በቀር አንዳች ትምህርት ቤት ያልሄደ፡ ወንድ ልጅ፡ በቤተ መቅደስ ውስጥ ፡ በእግዚአብሄር ቃል ላይ፡ ከክሃናት ጋር ሲነጋገር ተገኘ። በህጻኑ ልጅ ማስተዋል ሁሉም ተገረሙ። ለምን? እሱ ቃል ስለሆነ። አሁን ተመልከቱ።

76 እናንተን ማርያም የእግዚአብሄር እናት ለምትሉ ካቶሊካውያን ለማንቋሸሽ አይደለም፡ ግን እዚህ ጋር አንዳች ስህተት ላሳያችሁ። ቤተ ክርስትያን በማርያም ላይ የተገነባች ከሆነች፡ የተፈጠረውን ተመልከቱ። መጣችና "አረ፡ እኔ እና አባትህ፡ እያለቀስን ሰንፈልግህ፡" አለችው። አባባልዋ ተመልከቱት፡ ወድያው ምስክርነቷን ታወግዘዋለች። ያለችው፡ "አባትህ እና እኔ፡ አንተን እያነባን ፈለግንህ።"

77 ያንን ቃል አስተውሉበት። እሱ ቃል ነው። እንዲህ አላቸው፦ "በአባቴ ጉዳይ መሆን እንደሚገባኝ አታውቁምን? " ቃል ስህተት ሲያርም ተመልከቱ። በእነዚህ ሁሉ ክሃናት ፊት፡ ምስክርነቷን ከንቱ አደረገች። በመንፈስ ቅዱስ እንደጸነሰች

ተናግራ ነበር፡ አሁን ግን ዮሴፍ "አባቱ" ነው አለች። ያንን ቃል ወድያው ሲያጠምደው አያችሁ? ቃል ነበር እሱ። አሁን'ኮ፡ የአስራ-ሁለት-አመት ህጻን ልጅ ይሄን እንደማያደርግ ታውቃላችሁ። እሱ ቃል ነው። በዚያ ዘመን የተነገረ ህያው ቃል እሱ ነው፡ ስለዚህ የታወቀ የእግዚአብሄር ባህርይ በክርስቶስ ነበር። ስህተቶችን አረመ። እሱ አለ...

እነርሱ፡ "እንዴ፡ እኛ'ኮ የሙሴ ደቀ መዝሙርት ነን" አሉት። አያችሁ?

78 እንዲህም አላቸው፦ "ሙሴ ስለ'ኔ ጽፏል። የሱ ደቀመዝሙር ብትሆኑ፡ ባወቃችሁኝ ነበር። ሙሴስ፦ 'ጌታ አምላካችሁ እንደ'ኔ ያለ ነብዪ ያስነሳላችኋል' ብሏችኋልና። ሙሴንስ ብታውቁ እኔን ደግሞ ባወቃችሁ።"

79 አሁንም፡ እዩ፡ ቃሉ የዘመንን ስህተት ሁሌ ያርማል። ሰዎቹ ግን ሊያምኑ አይፈልጉም። በቃ ባሉበት ይደርቃሉ፡ በዚያ ይቀጥላሉ።

80 ኢየሱስ ግን የገዛ እናቱ እንኳን አርሟታል። እናቱ ተሳስታ ነበር፡ ምክንያቱ አስቀድማ በእሷ ውስጥ የተጸነሰው ልጅ በመንፈስ ቅዱስ ነው ብላ ተናግራለች፡ እዚህ ጋር ምስክርነቷን ዞር አደረገችና "አባቱ" ዮሴፍ ነው አለች፡ የኢየሱስ—— አባት ነው አለች። አሁን——ዮሴፍ...

81 ማለት የዮሴፍ ልጅ ከሆነ፡ በአባቴ ጉዳይ ላይ ነኝ ሲል፡ በእንጨት ስራው ላይ መሆን-ነበረበት።

82 እሱ ግን በአባቱ ስራ ላይ፡ በቤተ መቅደስ ውስጥ፡ እነዚያ የኃይማኖት ድርጅቶችን፡ እየገሰጸ ነበር። አያችሁት? የአስራ-ሁለት-አመት ጩቅላ ልጅ፡ በገዛ አባቱ ስራ ነበር። "በአባቴ ስራ ላይ መሆን እንደሚገባኝ አላወቃችሁምን? "

83 ኢየሱስ በሰይጣን በተፈተነ ጊዜስ አስተውላችኋል? በፈተናው ጊዜ፡ የነበሩ ባህርያቶቹ ሁሉ፡ አምላክ መሆኑ ያስታውቃሉ፡ ምክንያቱ ከቃሉ ጋር ጸንቶአል። አያችሁ? "ተጽፏል፡" ይለዋል ሰይጣን።

ኢየሱስም፡ "እንዲህም ደግሞ ተጽፏል፡" በማለት ለቃሉ ታማኝ ሆኖ ጸና።

84 "እግዚአብሄር፡ በብዙ ዓይነትና፡" እዚህ አነብበናል። "እግዚአብሄር፡ በብዙ ዓይነትና፡" በብሉይ ጊዜ እንደ ማለት ነው፡ "በብዙ ጎዳና፡" በተለያየ መንገድ፡ "እራሱን በነብያት በራእይ አስታውቋል።" የተናገረውን ነገር ሲፈጸም፡ የነብዪ ገጸ ባህርይ ይህ ነው። ስለዚህ አሁን እግዚአብሄር ከእርሱ ጋር የመኖሩ፡ የገጸ ባህርይው መታወቂያ ይሄው ነበር። ስለዚህ ይሄ የዘመኑ ቃል የሚተርጉምበት ስልጣን አስጠው፡ ምክንያቱ፡ "የእግዚአብሄር ቃል ወደ ነብያት ይመጣልና፡" አስቀድሞ የተነገረለት የነብዪ፡ ባህርይ።

85 መጽሀፍ ሲናገር፦ "አንዱ ተነስቶ፡ የተናገረው ነገር ቢፈጸም፡ እንግዲያውስ እሱን ስሙት፡ ነገር ግን፡ ባይፈጸም፡ አትመኑት፡ አትፍሩት፡ የእኔ... የእኔ ቃል—— በእርሱ አይደለም። ከተፈጸመ ግን፡ ቃሌ በእሱ ዘንድ ነው።" መታወቂያው ይህ ነው። የነብዪ ባህርይም ይሄው ነው።

86 ስለዚህ አሁን፡ እግዚአብሄር፡ እራሱን ለሰው የባህርያቱ መለያ የሚያሳይበት መንገድ፡ በብዙ ጊዜ የሚለው፡ ነብዪ ለመሆን በተጠራ ሰው በመናገር ነው። አሁን መጽሐፍ ሲናገር፡ "እግዚአብሄር፡ በብዙ ጊዜ፡ እና በብዙ ጎዳና፡ ለአባቶቻችን በነብያት ተናግሯል" ይላል።

87 በሁለተኛ ጴጥሮስም፡ የእግዚአብሄር ቃል በሙልሉ በእነሱ የተጻፈ እንደሆነ፡ እናነባለን። "ሽማግሌዎች፡ በምንፈስ ቅዱስ ተመርተው፡ መጽሀፍ ቅዱስን ጻፉት።" እነሱም ነብያት ነበሩ። ቃሉ ወደ እነርሱ ይመጣና፡ በመገለጥ ስር ሆነው፡ ይከትቡታል፡ይጽፉታል። አስቀድመው ነብያት መሆናቸው ይታወቃሉ፡ ከዚያ ቀጥለው—የመገለጥን ቃል ይጽፋሉ። እግዚአብሄር በውስጣቸው ስለሆነ የቃሉ መለኮታዊ ትርጉም ነበራቸው።

88 ስለዚህ አሁንም በመታወቂያው ባህርያት እራሱን የሚያሳይበት መንገድ ይሄው ነው፡ ራእዮቻቸው ሲረጋገጥ፡ እግዚአብሄር እራሱን ለህዝቡ በሚገልጥበት፡ በውስጣቸው በሚገኝ የሱ ባህርያት ነው።

89 ስለዚ፡ እሱ በክርስቶስ ውስጥ የነበረበት ብቸኛው መንገድ ይሄው ነው። ነብዩ ማለት ትንሽ ክፍል ነው። ክርስቶስ የእግዚአብሄር ሙላት ነበር። እግዚአብሄርም በክርስቶስ ሆኖ ዓለምን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበር። ባህርያቶቹም፡ ማን እንደነበረ ገልጸውታል፡ እንዲህ እስኪል ድረስ፦ "የአባቴ ስራ ካልሰራሁ፡ አትመኑኝ። ማለት የአባቴ ባህርይ ከሌለኝ፡ እንግዲያው አትመኑኝ፡ የእኔ ነገርም አትመኑ። በእኔ ውስጥ የአባቴ ባህርይ ከሌለ፡ እንግዲያውስ፡ ፈጽማችሁ፡ አትመኑት።"

90 የሱ ባህርይ፡ መቼም አይቀየርም። የበግ ጠቦት ባህርይ—መቀየር—እንደማይቻለው ሁሉ፡ እግዚአብሄር ባህርዩውን ሊቀይር አይችልም፡ ሌላ ነገር ሁሉ የገዛ ባህርይው መቀየር እንድማይቻለው ሁሉ። ምክንያቱ፡ ኦሪጂናል እስከሆነ ድረስ፡ ኦሪጂናል ነው። ስለዚህ፡ አንዳች ነገር ከቀየራችሁ፡ ኦርጂናልነቱን ቀይራችሁታል።

91 ይህ ማለት እርያን—ወስደው፡ እርያን ማጠብ እና—ጥፍሮቿን ቀለም መቀባት ዓይነት ነው፡ ሴቶች እንደሚያደርጉት፡ በሊፕስቲክ አስተካክላችሁ፡ ቆንጆ ቀሚስ አልብሷት። ከዚያ በኋላ አሮጊትዋን አሳማ ልቀቋት፡ በቀጥታ ጭቃው ውስጥ ለመዋለል ትሄዳለች፡ ደግማ ደጋግማ ትዋልላለች። ለምን? በቃ፡እርያ ናት። እና፡ ግን፡ ታውቃላችሁ፡ እናንተ ይሄን ማድረግ፡ የማይቻላችሁ ግን...

92 በግ ይሄን አያደርግም። ጭራሽም ጭቃ አጠገብ አይደርስም። ከጭቃው ጋር ጉዳይ የለውም። ባህርዩ ነው። አያችሁ? እሱንም በተመሳሳይ ልብስ ብታለብሱትም እንኳ፡ በርግጥ አያደርገውም፡ በርግጠኝነት አይሄድም። ውጨኛው ችግር የለውም፡ ዋናው ውስጠኛው ነው። ስለዚ አሁን፡ እግዚአብሄር የህይወት ሁሉ ምንጭ ከመሆኑ ጋር...

93 ይሄን መረዳት አይሳናችሁ። በውስጤ ባለው ሁሉ፡ አንዳች ነገር ማየት እንድትችሉ፡ እየጣርኩ ነው። 93 አያችሁ? ወዳጆቼ፡ ለእናንተ ጥቅም ነው። ስለ—እናንተም ነው። አያችሁ?

94 ለመታየት ብየ እዚህ ድረስ አልመጣሁም። ሌላ የሚኬድ ስፍራ ስለሌለም፡ ወደዚህ አልመጣሁም። ወደዚህ እንድመጣ ስለተመራሁ ወደዚህ መጥቻለሁ። ጌታ ለእኔ የሠጠው አገልግሎት እዚህ ስፍራ ባለ ህዝብ መታየት እንዳለበት ተሰማኝ፡ ስለዚህ አሁን እግዚአብሄር በትክክል ምን መሆኑን ማየት እንድትችሉ እየሞከርኩ ነው። ቃል የተገባው ቃሉ እሱ ራሱ ነው። እሱ ሁሌም ቃል ነው፡ እራሱንም በገባው ቃል ባህርያት መሰረት እራሱን ያስተዋውቃል። በአንድ ዘመን

ውስጥ፡ በቃል ውስጥ ከሚገኝ አንድ ባህርይ፡ ሊታይ ይችላል፡ ስለዚህ የዚህ የሚነሣው ሰው ባህርያቶች ሰውየው እርሱ መሆኑ እንዲታወቅ ያደርጉታል።

95 ኢየሱስ የሆነውን ሁሉ እንዲሆን የቻለበት ምክንያት ይሄው ነበር። ሊያዩት ይገባቸው ነበር። መታወራቸው አያስገርምም። ነገሩ... ተብሏል፡ በፊታቸው ብዙ ተአምራት አደረገ፡ ቢሆንም ማመን አልቻሉም፡ ምክንያቱ ኢሳያስ እንዳለው፡ “አይን አላቸው አያዩም፡ ጆሮም ግን አይሰሙም።” አያችሁ? ትውልድ ሁሉ፡ በእሱ ትውልድ ብቻ አይደለም፡ ነገር ግን ትውልድ ሁሉ፡ እንዴት፡ “እግዚአብሄር፡ ብዙ ጊዜና፡ በብዙ ጎዳና፡” አሁንም ሊገባቸው አይችልም።

96 ስለዚህ፡ ባህርዩ ፈጽሞ አይወድቅም። ሁሌም አንድ ነው። ይሄን፡ አስታውሱ፡ የእሱ ባህርያት፡ የእግዚአብሄር ባህርያት፡ አይወድቅም። ከወደቀ ግን፡ እግዚአብሄር ወድቋል። መጽሐፍ ቅዱስ በእብራውያን 13:8፣ ላይ ሲናገር፦ “ኢየሱስ ክርስቶስ ትላንትናና፡ ዛሬ፡ እስከዘለአለም ድረስ ያው ነው፡” ይላል። ስለዚህም፡ የማይቀያየር አምላክ ይባላል። በመጀመርያ ያለው የትኛው ዓይነት ባህርይ፡ እስካሁን ድረስ ያው ባህርዩ ነው። በየትኛው መልኩና፡ በየትኛውም ጊዜ የሰራው ነገር፡ ሁሌም ቢሆን በተመሳሳይ መልኩ የሠራዋል። ካልሆነ ግን፡ ባህርዩ ተቀየረ፡ አያችሁ፡ የገዛ ባህርዩ አምልካዊ ያልሆነ አንዳች ነገር አሳየ ማለት ነው። ስለዚህ ከየት እንደምናውቅ... ገባችሁ?

97 ጳውሎስም እንዳለው፦ “መለከት የተለየ ድምጽ ከሰጠ፣ መለከቱ የተለየ ድምጽ ከሰጠ፡ ለሰልፍ ማን ይዘጋጃል? ” መለከቱ “አፈግፍግ” የሚል ድምጽ ካወጣ፡ ማድረግ ያለብን ይሄው፡ ማፈግፈግ ነው። መለከቱ “አጥቃ” ከጮኸ፡ ማድረግ ያለብን ይሄው፡ ማጥቃት ነው። መለከት ምንድነው? የእግዚአብሄር ቃል ነው። ምን ይሁን—ምን “ወደፊት ሂድ፣ ቁጭ በል፣ አፈግፍግ፡ አነጣጥር” ሁሉንም፡ እግዚአብሄር የሚያስተዋውቅ ነው። የእግዚአብሄር መለከት ድምጽ ነው።

98 መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ እና እንዲያ ይሆናል ሲል፡ የተለየ ድምጽ ነው ይሉታል፡ አንዳንድ ሰዎች “አይ፡ ይሄ'ኮ፡ የሌላ ዘመን ነው፡” ይላሉ። ይሄው የተለየ ድምጽ ይሄው ነው። ምን ማድረግ እንደሚገባችሁ አታውቁም።

99 ኢየሱስ “ነፍሴ ላኖራትም እንደገና ላነሳትም ስልጣን አለኝ፡” ብሏል። እዚህ ላይ ያልተለመደ ድምጽ የለበትም።

100 ሴቲቱ፡ “መሲሑ እንዲመጣ እናውቃለን፡ እርሱ ሲመጣ፡ የሚያደርገውን ሁሉ እርሱ ይነግረናል” አለችው።

101 እሱም “እኔ እርሱ ነኝ፡” አለ። ይሄ ያልተለመደ ድምጽ የለበትም። “እኔ እርሱ ነኝ።” አሀ-ሀሀ! አሜን።

እነሱ “አባቶቻችን በምድረ በዳ መና በሉ” አሉት።

102 እሱም “ሁሉንም፡ አንድም ሳይቀር፡ ሞቷል፡” አላቸው። “እኔ ግን ከእግዚአብሄር ዘንድ ከሰማይ የወረድኩ የህይወት እንጀራ ነኝ፡” አላቸው። ያልተለመደ ድምጽ አይደለም። “የኤደን ገነት፡ የህይወት ዛፍ እኔ ነኝ።” በፍጹም፡ ያልተለመደ ድምጽ አይደለም። በትክክል አይደለም። አንዳች ያልተለመደ ነገር የለበትም። በሚያደርገው ነገር ሁሉ የጸና ነው።

103 መጽሐፍ ቅዱስ በድምጹ የእግዚአብሄርን ባህርያት ያሰተዋውቃል እንጂ። ያልተለመደ ድምጽ አይሰጥም።

104 በቅዱስ ዮሃንስ፡ 10:37 ላይ ኢየሱስ አለ፦ “የአባቴን ሥራ ካልሰራሁ፡ ምን... የአባቴም ባህርይ ከሌለኝ፡ እንግዲያውስ እኔን አትመኑ ብሏል። የሱ ባህርያቶች፡ በእኔ ውስጥ ባህርዪው እንዲታወቅ የሚያደርጉ፡ እነዚያ ናቸው።”

105 ምክንያቱም፡ አባት ቃል ነው፡ “በመጀመርያ ቃል ነበረ፡ ቃሉም በእግዚአብሄር ዘንድ ነበረ፡ ቃሉም እግዚአብሄር ነበረ፡” ስለዚህ የእግዚአብሄር ባህርይ በዘመኑ በተሰጠ ቃል ኪዳን ይንጸባረቃል።

106 እርሱ በሙሴ ዘመን ውስጥ ቢኖር ኖሮ፡ አይሰራለትም ነበር። እንዲሁም ሙሴ በእርሱ ዘመን ቢኖር፡ አይሰራለትም ነበር። በኖህም ዘመን የኖረ ቢሆን ኖሮ፡ ወይም ደግሞ ኖህ በእርሱ ዘመን ቢኖር፡ አይሰራለትም ነበር። ኖህ የዚያች ዘመን ነገሮችን በትንቢት ይናገር ነበርና፡ ባህርያቶቹ እና የሰራቸው ነገሮች ሁሉ በእግዚአብሄር ቃል ውስጥ እንዲታወቅ አደረገው። ሙሴ ያደረገውም ያው ነው።

107 እዚህ ጋር ደግሞ ኢየሱስ መጣ፡ ለዘመኑ የተሰጠ የተሰፋ ቃልም በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ አምላክ በሆነው በቃል ባህርያት፡ ታወቀ። አሜን።

108 በዘመኑ ፍጻሜ፡ የመንፈስ ቅዱስን በሰዎች ዘንድ፡ መፍሰስ፡ የእግዚአብሄር ባህርይ በሰዎች ዘንድ እንዲታወቅ አድርጓል። ቃል የገባለት ነበር። ቃል ነው። አደርጋለሁ ብሏል። ማንም አያደናቅፈውም። አደርጋለሁ ብሏል።

109 ስለዚህ እሱ ያደረጋቸው ነገሮች ሁሉ፡ እሱ እራሱ ቃል የገባቸው ነገሮች ናቸው። ይህም ባህርዩ ያሳያል። አዎን፡ ወዳጄ። “ባህርያቶቼ የእግዚአብሄር ዓይነት ካልሆኑ፡ እኔ ያልኩት አትመኑ፡ አትመኑት።”

110 አሁን በዮሃንስ 14:12 ላይ ተመልከቱ፡ “በእኔ የሚያምን፡” አለ፡ “የእኔ መታወቅያ፡ የእኔ ባህርይ ይኖረዋል። በእኔ የሚያምን፡ እኔ የማደርገው እርሱ ደግሞ ያደርጋል።” ይህም የእርሱን ባህርያት በመተረኩ፡ የክርስቶስ ባህርይ በእርሱ ውስጥ እንደሚገኝ ያስታውቃል። አሜን።

111 ብኀረንንም፡ በትክክል መንፈሳዊነት ተሰምቶኛል። አዎን፡ ጌታየ። ኦህ፡ ማይ! እያችሁ፡ ህይወቱ! ምንም ስህተት የለበትም! “በእኔ የሚያምን፡ እኔ የማደርገው እርሱ ደግሞ ያደርጋል።” አያችሁ፡ ይህ ባህርዪን ያሰተዋውቃል።

112 እግዚአብሄር—በእሱ ዘንድ ሆኖ፡ የተናገረው፡ “የእኔ ባህርይ እኔን የማያሳያችሁ ከሆነ፡” ስለዚህ እሱን... እሱን አትመኑት። በዚያም ጭምር እንደሚታወቅ፡ ተናግሯል። ይሄ፡ እሱን የማያሳውቅ ከሆነ ግን፡ እንግዲያውስ፡ እሱ አልተናገረማ።

113 ክርስቶስም፡ ዛሬ፡ እራሱን ካላስታወቀ፡ ቃሉን በማመን የክርስቶስ መሆናችን የምንታወቀው፡ በክርስቶስ ባህርይ ነው... ኢየሱስ ቃል ነበር፡ ስለዚ ቃሉን ማመን ነበረበት። እኛስ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እየካድን፡ የክርስቶስ ነን እንዴት እንላለን? ቅዱሱ የክርስቶስ መንፈስ ማለት እግዚአብሄር በእናንተ ውስጥ ነው፡ እርሱም ቃል ኪዳኑን ሁሉ “በአሜን” ሰርዓተ ነጥብ ይፈጽመዋል። መጽሐፍ፡ “ለሚያምኑ ይሄን ምልክት ይከተላቸዋል” ይላል። የእግዚአብሄር መንፈስም፡ “አሜን” ይላል። አያችሁ?

114 እንዳቸውም፡ “እይደለም ይሄ’ኮ፡ ለሌላ ዘመን ነው፡ ለሐዋርያት ብቻ ነው” አይሉም።

115 “ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ለፍጥረትም ሁሉ ወንጌልን ሰበኩ። ለእርሱ፡ በዓለም ከየትኛውም ቦታ፡ ለሚያምን ሁሉ፡ ያው ነው፡ እነዚህ ምልክቶች ይከተሉታል።” ባህርዩ የሚታወቅበት፡ “ትላንትናና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘለአለም ድረስ ያው ነው።”

116 ይህም እብራውያን 1:1 ያጸናል፡ “እግዚአብሄር ብዙ ጊዜ፡ አባቶቻችንን በነብያት ተናግሮ፡” ክርስቶስ ዛሬ፡ በትንሳኤው፡ ብዙ ጊዜ ባደረጋቸው ተመሳሳይ ባህርያት፡ እንዲታወቅ ያደርጋል። አስተውላችኋል? እግዚአብሄር አሰራሩን ፈጽሞ አይቀይርም።

117 መጽሐፍ ቅዱስ በብሉይ፡ ሕልም አላሚው ሲያልም፡ ህልሙ ትክክል ይሁን የተሳሳተ የሚመረምር ነብዪ በምድሪቱ ከሌለ፡ ሌላ የሚያውቁበት መንገድ ነበራቸው። ህልሙ ማንም ይየው፡ ወደ ቤተ መቅደስ ይወስዱት ነበር፡ ይሄን ዓይነት ባህርይ ነበራቸው። በሊቀ ካህኑ፡ በአሮን ደረት የነበረው ፈርጥ፡ ግድግዳ ላይ ይሰቀላል። ከዚያ ህልም አላሚው ህልሙ ይናገራል። ምንም ያህል መልካም፡ እና እውነት ቢመስልም፡ ኡሪም እና ቱሚም የሚባሉ ድንጋዮች፡ መለኮታዊ ብርሃን ካላንጸባረቁ (መጽሀፍ ቅዱስ አንባቢዎች ይገባቸዋል)፡ ምንም ያህል ትክክለኛ ቢመስል ግድ አይሰጠኝም፡ እውነት የለውም። የማይለመደው እምላክነቱ፡ የእግዚአብሄር ባህርይ፡ በመለኰት ላይ ባህርዩን ማሳየት ይኖርበታል፡ ይህም ከተነገረው መልዕክት ጋር እርሱ መኖሩ ለማሳወቅ ነው። አሜን።

118 ዛሬም እኔ አንድ አይነት ነገር እላለሁ። የጥንቱ ኡሪም እና ቱሚም አሁን የለም፡ ነገር ግን አሁንም የእግዚአብሄርን ባህርይ የሚያሳውቅ ቃል፡ በዘመናችን ውስጥ የተገባው ተሰፋ ቃል ነው። አሁን እኛ እየኖርንበት ባለው ዘመን ውስጥ ባለው ተሰፋ ቃል ውስጥ የእግዚአብሄር ባህርያት ተለይቶ ይታወቃል።

119 ይህም እግዚአብሄር እንደ ድሮው አሁንም ያው ያደርገዋል። “በብዙ ጊዜና፡” ተመልከቱ፡ “በብዙ ጎዳና፡ ለአባቶች በነብያት ተናግሯል።” “ህግ እና ነብያትም እስከ ዮሃንስ ድረስ ነበሩ፡ ከዚያ በኋላ፡ የሰማይ መንግስት።” አስተውሉ፡ “በዚህ የመጨረሻ ዘመን ግን፡” ያኔ ያደረገውን ነገር፡ “በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ” እየተናገረ ይገኛል። “እግዚአብሄር፡ በብዙ ጊዜና፡ በብዙ ጎዳና፡ በዚህ በመጨረሻ ቀናት፡ ለአባቶች በነብያት ተናገረ፡” አሁንም ተመሳሳይ ነገር ያደርጋል፡ “ህዝቡን ሁሉ (አባቶችን) በክርስቶስ ኢየሱስ በልጁ” እየተናገረ ነው። ከሞት እሱን አስነሳው፡ ልዩ ልዩ ነገሮችን እየነገረን፡ እራሱን ከእኛ ጋር እያስተዋወቀ በእኛ ውስጥ እየኖረ ነው፣ የልብን አሳብ እና መነሻ የሚመረምር እሱ እንደሆነ። ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት እና ዛሬ፣ እስከ ዘለአለም፣ ድረስ ያው ነው! “እግዚአብሄር፡ በብዙ ጊዜ እና በብዙ ጎዳና ለአባቶች በነብያት ተናገረ፣ በዚህ በመጨረሻ ዘመን ግን በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል።” ቅዱስ ቃል አይስነጣጠቅም። ትክክል ነው።

120 አስቀድሜ እንዳልኩት፡ እግዚአብሄር ይሄንን ቃል እንዲተረጉምለት ማንንም አይፈልግም። የገዛ ቃሉ እራሱ ይተረጉማል። እሱ ምንም ነገር ሲናገር፡ የተናገረው ይፈጸማል፡ ትርጉሙም ይህ ነው። አያችሁ? ማንም ሰው፡ “እዎን፡

**እንዲህ** ለማለት እንደፈለገ አምናለሁ" እንዲል አይፈልግም። እግዚአብሄር በገዛ እራሱ ትርጓሜ ያተዋውቃል።

121 ይህ፡ ተሰፋው ለዚያች ዘመን የተመደበ ከሆነ፡ እኛ በሉተር—ብርሃን— ውስጥ መኖር አይቻለንም፣ በዌስሊ ብርሃን መኖር አንችልም፡ ባማንኛቸው ብርሃን ውስጥ መኖር አይቻልም። ለዚህ ዘመን በተሰጠ የተሰፋ ቃል ብርሃን ውስጥ መኖር አለብን።

122 እስኪ ሙሴ ወደ ግብጽ ወርዶ፡ እንዲህ ቢልስ፦ "መልካም፡ ትልቅ መርከብ እንገንባ። ከዚህች አገር ተንሳፍፈን እንወጣለን። ናይል ወዲህ ይፈሳልና ቢልስ"? ብራናዎቹ ወደኋላ ይመረምራሉ፡ እንዲህ አይነት ተሰፋ ቃል የለም። አዎን። አያችሁ፡ የተናገረው ግን፡ ስለተፈጸመ፡ እንደ እግዚአብሄር ነብዩ ታወቀ፣ እነሱም የጌታ ቃል በእሱ ዘንድ እንዳለ አወቁ። ፈርኦን ጦር ነበረው፡ ሙሴ ግን የእግዚአብሄር ቃል ይዞ ነበር። ወደ ባህሩ በመጡ ጊዜ፡ ጦር ሁሉ ወደ ባህር ሰመጠ፡ ሙሴ ግን እስራኤልን ከባህሩ ማዶ፡ ወደ ደረቅ ምድር አሻገራቸው፡ ምክንያቱ ቃል ስለነበረው፡ እሱ እራሱም የዘመኑ ቃል ነበር። ሙሴ እራሱ ለዚያ ዘመን የተገለጠ ቃል ነበረ።

ኤልያስ እራሱ ለዚያ ዘመን የተገለጠ ቃል ነበረ።

123 ክርስቶስም የተገለጠው ቃል እና እሱ የገባቸው ተሰፋ ቃል ነበር። "ጥቂት ጊዜ አለ ዓለም አያየኝም፡ እናንተ ግን ታዩኛላችሁ፡ እኔ ከእናንተ ጋር እሆናለሁና፣ በእናንተ ውስጥም፡ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ። እኔ የማደርገውን ሥራ እናንተ ደግሞ ታደርጋላችሁ።" እሱ እነዚህን ተሰፋ ቃሎች ሰጥቷል። ምንድነው? በሌሎች ዘመናት ሁሉ እንዳደረገ፡እግዚአብሄር የገዛ ቃሉ ወደ ትዕይንት የሚያቀርብበት ባህርይ ነው።

124 ሚልኪያስ 4፡ እንዲህ አለ፦ "ታላቁ እና የሚያስፈራው የጌታ ቀን ከመምጣቱ በፊት፡ እነሆ፡ እኔ ነብዩ ኤልያስን ወደ እናንተ እልካለሁ፡ እርሱም ከዚያ ቀን አስቀድሞ፡ የልጆችን እምነት እንደገና ወደ አባቶች ይመልሳል።" እርሱ ቃል ገብቷል።

125 ኢየሱስ፡ በሉቃስ 17ኛ ምዕራፍ እንዲህ ብሏል፡ "በሰዶም ዘመን እንደ ሆነ፡ የሰው ልጅ በሚመጣበት ዘመን፡ የሰው ልጅ በሚገለጥበት ዘመን እንዲሁ ይሆናል።" መገለጥ በራሱ በሚከፈትበት፡ ዓለም ሰዶምን በምትመሰልበት ዘመን፡ ምን ሊሆን ይሆን? የዚያች ቃል ባህርይ በሚፈጸምበት። እግዚአብሄር በራሱ ባህርይ፡ አስቀድሞ በነበረው ባህርይ እራሱን ያስተዋውቃል። ይሄን ሊተው አይቻለውም።

126 በመጨረሻው ቀናት፡ እራሱን በልጁ በኩል አስተዋወቀ። እግዚአብሔር እነዚህን ሁልጊዜ እንዴት እንደሚያደርጋቸው አስተውሉ... እሱ አደ-... አደራረጉን ፈጽሞ አይለውጥም።

127 በሰዶም ዘመን በዚያ ስንነጋገር እንደነበርን፡ እነዚህ ሦስት ሰዎች፡ ከአብርሃም ጋር ተነጋገሩ።

128 አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ። እግዚአብሔርን በቃሉ የተቀበለው ሰው ነው። እግዚአብሄር እርሱን በጠራው ጊዜ፡ ሚስቱ፡ ሳራ፡ የሰድሳ አምስት ዓመት፡ አብራሃምም የሰባ-አምስት ዓመት ነበሩ። እርሱም ልጅ—እንደሚወለድላቸው፡

አብራሃምን ከሳራ ልጅ ታገኛለህ አለው። ትንሽ ከባድ ሊመስል ይችላል፡ ነገር ግን—ሚጢጢ ጫማ እና አሻንጉሊት እንደያዘች አስባለሁ፣ ልጁን ለመቀበል፡ በሌላ ነገሮችም ጭምር፡ ተዘጋጅታለች።

129 ከመጀመርያዎቹ ሀያ-ሰምንት ቀናት በኋላ፡ ማለት፡ ምናልባት አብራሃም ለሳራ "ምን እየተሰማሽ፡ የኔ ማር? " ብሏት ይሆናል፡

"ልዩነት የለም።"

"ክብር ለጌታ፡ ምንም ቢሆን፡ መውለዳችን አይቀሬ ነው።"

"እንዴት ታውቃለህ? "

"ጌታ ስለተናገረ።"

አንድ አመት አለፈ። "ምን እየተሰማሽ፡ የኔ ማር? "

"ልዩነት የለም።"

"ምንም ቢሆን፡ መውለዳችን አይቀሬ ነው። ጌታ ተናግሯልና።"

አምስት አመታት አለፉ። "አሁንስ ምን እየተሰማሽ ነው፡ ዉዴ? "

"ልዩነት የለም።"

"ምንም ቢሆን፡ መውለዳችን አይቀሬ ነው። ጌታ ተናግሯልና።"

130 ምን ስለነበረ ነው? የእግዚአብሄር ቃል ኪዳን ስለነበረ። እግዚአብሄርን አምኖ፡ እንደ እግዚአብሄር ተንቀሳቀሰ፡ ኪዳን በተገባለት ቃል ላይ የሙጥኝ አለ። ያውም...

131 ሀያ-አምስት አመታት አለፉ። ጫማዎቹ ቢጫ እስኪሆን ተቀያይሯል፡ አሁንም ግን የሙጥኝ ብላለች። እሱም አርጅቷል፡ ጎብጧል፡ ቅርጹ እጅጉን ተበላሽቷል፡ መክኗል፡ የሳራ ማህጸን ጨርሶ ሞቷል። አቤት የነበሩበት ገጽታ!

132 አሰመሳይ-አማኞች ጓደኞቹም "እንዴት ነህ፡ አብራሃም፡ የህዝቦች አባት? " ይሉታል።

133 "ደህና፡ ክብር ለጌታ ይሁን፡ እኔ ደህና ነኝ። ምንም ቢሆን፡ ያን ልጅ መውለዳችን አይቀሬ ነው።" በአለማመን ከእግዚአብሄር ቃል ኪዳን ሳይንገዳገድ፡ እግዚአብሄር እንደተናገረ፡ እግዚአብሄርም ማድረግ እንደሚችል ፈጽሞ አምኖ፡ ለጌታ ክብርን እየሰጠ፡ በረታ። አሜን። እነሆ የአማኝ ባህርይ ይሄው ነው።

134 እናንተስ? እያችሁ? እኛ፡ የአብርሃም ልጆችስ? እንደ ቃል ኪዳኑ፡ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ታውቀናልን፣ ባህርያችንስ፡ በርግጥ እንዳመንነው እኛን ይገልጠናልን? ወይስ፡ **በዚህ** ጉዳይ ላይ፡ **ከዚህ** ዘለን፡ ወዲያ ማዶ፡ እና **ወዲህ** ወደታች፡ ፈራ-ተባ እያልን፡ እና በግምት፡ እና ፈራ-ተባ በማለት ነን? እንግዲያውስ፡ ክርስትያኖች አይደለንማ፡ አሰመሳይ አማኞች ነን።

135 ለተሰፋው ቃል፡ የጸናን ከሆንን ግን፡ አጥብቀን ቆመን እንጠብቅ! አብራሃም ጠብቋልና።

136 እንደምናውቀው፡ አንድ ቀን ሦስት ሰው እያዘገሙ፡ ሲመጡ ተመለከተ። እዚህ ጋር መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር፦ "በጠራራ ቀን ላይ" ይላል፡ ከከሰዓት ሳይሆን አይቀርም። እና ሰዎቹ ቀርበው አነጋገሩት። ሁለቱ ወደ ሶዶም

መውረዳቸውን እናውቃለን። አንዳቸው ግን ከእርሱ ጋር ቆየ። ባለፈው ማታ እንደተነጋገርንበት አምናለሁ።

137 ይሄ ከሱ ጋር የቀረው ሰው... እሱን የጠራ ሰው፡ ምን እንዳደረገ አስተውሉበት። አንደኛው ኤሎሂም እንደሆነ፡ በገዛ ባህርያቶቹ ይታወቃል።

138 ኤሎሂም፡ የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመርያው ቃል፡ "በመጀመርያ እግዚአብሄር... " አሁን፡ እናንተ ምሁራን የሆናችሁ ሁላችሁ **እግዚአብሄር** የሚለው ቃል፡ በእብራይስጥ፡ "ኤሎሂም" ማለት እንደሆነ ታውቃላችሁ፡ ትርጓሜውም፡ "ኃያል፡ አንዳች-የማይታጣው፡ በራሱ-የሚኖር" ማለት ነው፡ በራሱ የሚያደርግ፡ ከሌላም ረድኤት የማይሻ፡ የማንም ትርጓሜ የማያስፈልገው ነው። እሱ አንዳች-የማይታጣው፡ በሁሉ ስፍራ የሚገኝ፡ ሁሉን የሚያውቅ፡ ምንም የማይሳነው። አምላክ ነው።

139 እና እሱ መጣ። ይህ ቃል የሙጥኝ የያዘ ፓትሪያሪኩ፡ አብርሃምም አሁን፡ ይሄን ሰውየ ትኩር ብሎ ተመለከተው። ይሄ ሰውየ ጀርባውን ለድንኳኑ ሰጥቶ፡ "ሚስትህ ሳራ፡ የት ናት? " ብሎ ጠየቀው፣

"ከበስተጀርባህ፡ በድንኳኑ ውስጥ ናት" አለው።

140 "የዛሬ አመት እጎበኝሃለሁ፡ እኔ ለአንተ ቃል የገባሁትን ይህን ህጻን ልጅ ታገኛለህ" አለው።

141 ሳራም በዚህ ጉዳይ ላይ ሳቀች። እና ይህ ከእሱ ጋር የሚነጋገር ሰውየ፡ ሳራ በድንኳን ውስጥ፡ ከበስተጀርባው ሆና የተናገረችውን ነገር ነገረው።

142 ይሄን፡ በዘፍጥረት፡ ታነቡታላችሁ። ከዚያ በኋላ፡ ይህ ሰው እራሱን ካስተዋወቀ በኋላ፡ አብርሃም እናየዋለን...

143 ምንድን ነው የነበረው? ዕብራውያን፡ 4ኛ ምዕራፍ፡ 12ኛው ቁጥር፡ "የእግዚአብሄር ቃል የተሳለ ነው ይላል፡ ሁለት-አፍ ካለው ሰይፍ ይልቅ የተሳለ ነው፡ የልብን አሳብ እና ስሜት የሚመረምር ኃይለኛ ነው።"

144 ይህ ሰውየ እራሱ እንደሆነ ሲያውቅ እናየዋለን። ከሱ በቀር ሌሎች ነብያት በምድሪቱ እንዳልነበሩ ያውቃል፡ ስለዚህም ደግሞ የጌታ ቃል ወደ እርሱ መጣ። እና እሱ ነብዩ ነበር፡ ስለዚህም ቃል ወደ ነብዩ ይመጣል።

145 የመጥምቁ ዮኃንስም ተመሳሳይ ነው። ለአራት መቶ አመታት ነብዩ አልነበረም። እኔ አስታውሳለሁ...

146 ሽማግሌው ዶክተር ዴቪስ፡ ምናልባት እዚህ ቁጭ ብሎ ይሆናል፡ በዚህ እምነት ላይ እኔን ያጠመቀኝ ሽማግሌው የባፕቲስት ሚሽነሪ ሰባኪ። ከእኔ ጋር ሲሟገት ነበር። "ቢሊ አንተ'ኮ ገና ህጻን ልጅ ነህ። እኔን ማዳመጥ አለብህ፡" አለኝ።

"እሺ፡ ወንድም ዴቪስ፡ እየሰማሁህ ነኝ፡" አልኩት።

147 እንዲህ አለኝ፦ "እየህ፡ ዮኃንስ አልተጠመቀም። ሌሎችን ያጠምቅ ነበር፡ እሱ እራሱ ግን አልተጠመቀም፡ እሱን ማጥመቅ የሚችል ብቃት ያለው ሰው አልነበረም አለኝ።" ጥሩ የባፕቲስት ቲኦሎጂ ነው። "ኢየሱስ ወደርሱ ሲመጣ፡ ያኔ የተናገረው... ዮኃንስ ሲናገር፦ 'እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል፡ ለምን ወደ እኔ ትመጣለህ? ' እሱ ግን፦ 'አሁንስ ፍቀድልኝ'" አለው። "እና

‘በፈቀደለትም’ ጊዜ፡” አለኝ፡ “አየህ፡ ከዚያ ኢየሱስ ዮሃንስን አጥምቆታል። አለኝ፡ ከዚያ በኋላ ከውኃው በወጣ ጊዜ፡ ሰማያት ተከፈቱ እግዚአብሄርንም እንደ እርግብ አምሳል፡ ‘እኔ በእርሱ የምኖርበት፡ የምወደው ልጄ ይህ ነው፡’” እያለ፡ ወደሱ ሲመጣ አየ። አይደለም፡ ከዶክተር ዴቪስ ጋር ላለመስማማት ባይሆንም፡ እንዲህ ግን አይደለም፡ ተሳስቷል።

148 እያችሁ፡ ቃል ሁሌም ወደ ነብዪ ይመጣል፡ ዮኃንስ ነብዪ ነበር። ስለዚ ቃል ስጋ ቢሆንም፡ ወደ ነብዪው መምጣቱ፡ የማይቀር ነው፡ ምክንያቱ፡ ስለ ቃል ይመሰክራል፡ ባህርዩውም እንዲሁ እንደሆነ አስተዋውቆታል። አሁን ቃል መጣ፡ ከዚያስ ምን ሆነ? ወደ ኢየሱስ ፊት እንደቀረበ፡ ዮኃንስ እንዲህ አለ፦ “እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል; እንዴትስ አንተ ወደ እኔ ትመጣለህ? ”

149 ኢየሱስም፦ “አሁንስ ፍቀድልኝ፡ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና (ያስፈልገናልና)” አለው። ዮሃንስ እንደ ነብዪ፡ እሱም እንደ ቃል። እሱ መስዋዕት ነበር፡ ወደ ምድራዊ አገልግሎቱ ለመግባትም እያመቻቸ ነበር፡ መስዋዕት ከመቅረቡ በፊት መታጠብ ነበረበት። ዮሃንስ ይሄን ስለሚያውቅ፡ አጠመቀው። “አሁንስ ፍቀድልኝ፡ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና።” መስዋዕት ከመቅረቡ በፊትም መታጠብ አለበት፡ ስለዚህ ዮሃንስ አጠመቀው። ኢየሱስ አይደለም ዮሃንስን ያጠመቀው። ዮሃንስ ኢየሱስን አጠመቀው። “አሁንስ ፍቀድልኝ።”

150 እዚህ ጋር፡ አስተውሉ፡ የጌታ ቃል ከአብራሃም ጋር ነበር። የጌታ ቃል ወደሱ መጣ። ነብዪ ነበር። ስለዚህ ቃሉ መጣ። **አብራም** ሳይሆን፡ “አብርሃም፡” ብሎ ጠራው።

151 ከጥቂት ቀናት በፊት፡ ስሙ አብራም—አብራም ይባል ነበር፡ አሁን ግን አብርሃም ተባለ። ሚስቱም ሦራ ትባል ነበር፡ አሁን ግን “ሳራ፡” ሦ-ራ፡ ሳትሆን ሳራ ተባለች። (አ-ብ-ር-ሃ-ም) አ-ብ-ራ-ም ሳይሆን፡ አ-ብ-ር-ሃ-ም፡ አብርሃም።

152 ስለዚህ ይህ ሰው “አብርሃም!” ባለው ጊዜ፡ እራሱን አስተዋውቋል፡ ኦህ፡ ማይ!

አብርሃምም አለው፡ “ኤሎሂም!”

153 ነብዪ እና ቃልን፡ በአንድነት ተገናኙ፡ የሁለቱ ባህርይ ታወቀ።

154 ኤሎሂም፡ “ሚስትህ ሳራ ወዴት ናት? ” አለው፡

155 እሱም፡ “ከበስተጀርባህ፡ ድንኳን ውስጥ አለች” አለው። ከዚያ በኋላ… ተአምር ሆነ። ኤሎሂም! አብርሃም እሱን፡ “ምንም-የማይሳነው፣ ኃያል፣ ሁሉን የሚያውቅ አምላክ” ብሎ ጠራው።

156 ኢየሱስ በምድር ሳለ፡ ኤሎሂም የሰራቸው ነገሮች ሁሉ እኔ አድርጌአለሁ፡ ብሏል። ይሄም እሱ አምላክ እንደሆነ በባህሪዎቹ እንዲታወቅ ያደርገዋል።

157 እንዲህም ብሏል፡ አስቀድሞ፡ “ከመጨረሻዎቹ ቀናት በፊት፡ በሰው ልጅ መምጫ ጊዜ፡ እሱ በሚገለጥበት ወቅት፡ በሰዶም እንደነበረ ሁሉ፡ ይህ ነገር በድጋሚ ይሆናል አለ።” ይህም ኤሎሂም፡ ኃያሉ አምላክ እራሱ ከህዝቡ ጋር መሆኑ ያሳያል። ቅዱስ ቃል ይህ ነው። ኤሎሂም ከህዝቡ ጋራ ብሏል!

158 ለአርባ አመታት ያህል በኤሎሂም፣ በእግዚአብሄር፡ በመንፈስ ቅዱስ ሲያጠምቀን ኖሯል! ቤተ ክርስትያኒቱም…

159 ተመልከቱ፡ አብርሃም አንድ ምልክት አየ፡ ሌላ ጥሪ፡ ምልክት፣ ጥሪ፤ የተሰፋው ቃል ልጅን እየጠበቀ፡ ጥሪ፡ ምልክትን አየ። ይህ ለመጨረሻ ጊዜ ያየው ምልክት፡ የመጨረሻው ትዕይንት፣ የተሰፋው ቃል ልጅ ከመወለዱ በፊት የነበረው የእግዚአብሄር የመጨረሻው ጉብኝት፣ ኤሎሂም በሰው ስጋ መገለጡ ነው። ወዲያው የቃል ኪዳን ልጅ መጣ።

160 ስለዚህ የአብርሃም ዘር፡ የቃል ኪዳን ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን በመጠባበቅ ላይ ነው። ስለዚህ አሁን ምልክቶችን አይተዋል፡ ማለት የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ፡ በልሳን መናገር፡ መለኮታዊ ፈውስ፡ ወዘተ አይተዋል። የሰው ልጅ ሲገለጥ ግን፡ ኤሎሂም ወደ አብርሃም ዘውዳዊ ዘር ዳግም ይመጣል ያኔ ያደረጋቸው ነገሮች ሁሉ ዳግም አድርጎ ያሳየዋል፣ አሜን፡ ኤሎሂም፡ እንደ ቀድሞ! ለምን? የእግዚአብሄር ባህርይ ስለሆነ።

161 እንግዲያውስ፡ ክርስቶስ እግዚአብሄር ከነበረ፡ "ጥቂት ጊዜ አለ ዓለም አያየኝም፡ እናንተ ግን፡ እስከፍጻሜ፡ እስከ መጨረሻው ድረስ፡ እኔ ከእናንተ ጋር እና በእናንተ ውስጥ ስለምሆን፡ ታዩኛላችሁ። እኔ የማደርገው ስራ ሁሉ እናንተ ደግሞ ታደርጋላችሁ።"

162 ኢየሱስ ይሄን ነገር—በሉቃስ፡ 17ኛው ምዕራፍ ላይ ተናገረ። በጣም ጥሩ፡ ይህ መጨረሻው ዘመን ካየን እና ካመንን፡ ይህ ሁሉ እንደገና ሊፈጸም እየተመቻቸ ነው።

163 ስለዚህ፡ ዕብራውያን 1:1፣ "እግዚአብሄር፡ በተለያዩ ዘመናት፣ እና በነብያት እራሱን አስተዋውቋል፣ በዚህ በመጨረሻው ዘመን የልጁን ከሙታን መነሣት አስተዋውቋል፡" ይህም ያኔ የነበረው ያው ባህርዪው ለቤተ ክርስትያኒቱ በመስጠት፡ ዕብራውያን 13:8ን በትክክል በማስተካከል ነው።

164 አንዳች ላባ አትነቀልባቸውም። የንስር ላባዎች ናቸው። ሰማያዊ አእዋፋት ስለሆኑ፡ አጥብቀው ይጠብቃሉ። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ]... እሱም የንስር ምግብ ይመግባቸዋል።

165 አሁን ያንን፡ "በተለያዩ ዘመናት፣ በልዩ ልዩ መንገድ፣ ለአባቶች በነቢያት፣ በመጨረሻው ዘመንም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከሙታን በማስነሳት መናገሩ እናስተውላለን።" እነሆም እርሱ በእኛ መካከል ነው፡ ከሁለት ሺህ ዓመታት በኋላ፡ ራሱ ኢየሱስ ነው እንጂ፡ ከነቢያት አይደለም፡ የተነሣው የእግዚአብሄር ልጅ፡ ኢየሱስ ነው፡ ሀሌሉያ!

166 አንድ ቀን እንዲህ አለ፡ ኢየሱስ፡ እንዲህ አለ፦ "ክፉ እና አመንዝራ ትውልድ ምልክትን ይሻል፡ ምልክትም ይሰጣቸዋል።" ክፉ እና አመንዝራ ትውልድ። ዓለም የከፋበት፣ ወይም አመንዝራ የሆነበት፣ ወይም ከአሁን በላይ የተበላሸበት ዘመን መቼ ነው?

167 "በዮናስ ዘመን እንደ ሆነ፡ ዮናስ በአሳ አንበሪ ሆድ ውስጥ ሶስት ቀን እና ሌሊት እንደነበረ፡ የሰው ልጅም በምድር ልብ ውስጥ ሶስት ቀን እና ሌሊት ይሆናል።"

168 ከዚያስ፡ "ክፉ እና አምንዝራ ትውልድ" ምልክትን ይቀበላል። ምን ዓይነት ምልክት? የትንሳኤ ምልክት። ይሄው ዛሬ፡ ከሁለት ሺህ አመታት በኋላ እኛ ተቀብለናል፡ እሱ እስከ አሁን ድረስ ህያው ነው። ዛሬም፡ በእግዚአብሄር

ባህርያቶች እራሱን እያስተዋወቀን፡ ትናንትናና፡ ዛሬ፡ እስከዘለአለም ድረስ ያው ሆኖ፡ በእኛ ዘንድ አለ፣ በዚህ ዘመን አደርገዋለሁ ያለውን ቃል እየተረከ ይገኛል። አሜን።

169 ቃሉ ይሄውላችሁ። ምልክቱንስ ታምናላችሁን? ቀጣዩ ጉዳይ፡ በዘመኑ ፍጻሜ፡ በልጁ በኩል መታወቁ ነው። አስተውሉ።

170 እግዚአብሄር ሙሴን በተለያየ ጊዜ ተናግሮታል። በዘዳግም 18:15; እንዲህ አለ፦ "ጌታ አምላካችሁ እንደ እኔ ያለ ነብዪ ያስነሣላችኋል።" ተመልከት አሁን። ቃል ማለት ይሄ ነው። ቃል ነው። እግዚአብሄር ነው። ሙሴ አይደለም። ሙሴ እንዴት ይሄን ሊያውቅ ይችላል? ሙሴ ሰው ነው። እግዚአብሄር ግን፡ በሙሴ በኩል፡ እንዲህ ተናገረ። ታምናላችሁ? እሺ።

171 አሁን ኢየሱስን አስተውሉበት፡ የራሱ—ባህርያቶቹ ቃል ኪዳኑ እውነት እንደሆነ አስተዋወቁ። በርግጥም አድርጓል። ሙሴ ይሆናል ብሎ ያለውን ነገር በራሱ ባህርያት እሱ እንደሆነ አስታወቀ።

172 ዛሬ ብዙዎቻቸው፡ የሚፈልጉት፡ ታላላቅ መሪ ማየት ነው። "እረ፡ ይሄ'ኮ ፒኤች ዶክተር ነው። **እንዲህ-እና-እንዲያ ነው።** እሱ'ኮ ከሀርትፎርድ ዩኒቨርሲቲ ነው።" ወይም "ከመሳሰሉ ታላላቅ ሰፍራዎች ነው።" የእግዚአብሄር መታወቂያ ይሄ አይደለም። አይ፡ አይደለም። ቅንጣት ታክል አይደለም። እግዚአብሄርን የሚያስተዋውቀው ቃሉ ነው። እያችሁ?

173 ኢየሱስ ምሁር አልነበረም፡ ወይም ካህንም አልነበረም፡ ወይም ለዓለም፡ መምህር አይደለም። ይልቅ እሱ ለዓለም፡ ከሃዲ ነበር።

174 እግዚአብሄር ግን ቃሉን በእርሱ ዘንድ ያጸና ነበር፡ ይህም አማኑኤል አስደረገው። መታወቂያው ይህ ነበር። አሁን፡ እዚህ ጋር፡ እግዚአብሄር በሙሴ በኩል በተለያየ ጊዜ አደርጋለሁ ያላቸው፡ እሱ የሚያደርጋቸው፡ ኢየሱስ በትክክል አሟልቷል።

175 አሁን ባለፈው በድራማዊ አቀራረብ እንዳደረግነው፡ ጴጥሮስ ጋር፡ ጴጥሮስን አግኝቶ የጴጥሮስ ስም ማን እንደሆነ ሲነግረው ተመልከቱ። ይህ ምልክት ለጴጥሮስ፡ የመሲሁ መታወቂያ ያስረዳል። ምክንያቱ ቃሉ ሲናገር፦ "ጌታ አምላካችሁ ነብዪ ያስነሳላችኋል ይላል።"

176 እና ጴጥሮስ መጣ፡ ያኔ ስሙ ስምዖን ነበር፡ እሱ ወደ ነበረበት መጣ። ኢየሱስ እርሱን አይቶ፡ "ስምህ ስምዖን ነው፡ የዮና ልጅ ነህ" አለው። ይህ ነገር ሙሴ የተናገረው ተስፋ ቃል እሱ እንደሆነ የክርስቶስን ባህርይ አስታወቀ። ጴጥሮስም ይህች ምልክት ኢየሱስን እንደ መሲህ እንደምታስተዋውቀው አስተዋለ። እግዚአብሄር ለመጨረሻው ዘመን በተቀባው፡ "በክርስቶስ ዘንድ ነበረ።" ጴጥሮስን ሰሙ እንደነገረው፡ አስታውሱ። ለናትናኤልንም...

177 አሁን ደግሞ፡ ናትናኤልን ተመልከቱት፡ የሰራውን ሁሉ ነገረው። "ከበለስ ዛፍ በታች አየሁህ።" ይሄ እንደ መሲሕ ያስተዋውቀዋል።

178 "አንተ የእግዚአብሄር ልጅ ነህ። አንተ የእስራኤልል ንጉስ ነህ፡" አለው። እሱ መሲህ እንደሚሆን ቃል በተገባው ተሰፋው ቃል ባህርያት ታወቀ። "ጌታ አምላካችሁ ነብዪን ያስነሣላችኋል።"

179 በውኃው ጉድጓድ አጠገብ የነበረች ሴት፡ ምን እንደሆነች ነገራት፡ ይህም እሱ ተሰፋ የተደረገበት መሲህ እንደሆነ ያስተዋውቀዋል። አያችሁ?

180 የእሱ ባህርይ፡ ባህርያቶቹ፡ አስቀድሞ የሚታወቀው ቃል ነው። ባህርያቶቹ ቃል ማለት አምላክ እንደሆነ አሰይቷል፡ ስለዚህም ነው እግዚአብሄር በክርስቶስ የታወቀው። አሁን እዩት። አስምሩበት።

181 ለጴጥሮስ፡ ስሙን በመጥራት ለጴጥሮስ ታወቀ። ናትናኤልንም ያደረጋቸው ነገሮች በመናገር ታወቀለት። ማን እንደነበረች በመናገሩ፡ በሴቲቱ ታወቀ። እሱ ማን... **እሱ** ማን እንደሆነ፡ **እሱ** ምን እንዳደረገ፡ እና **እሷ** ምን እንደነበረች። የመሲሕ ባህርይ እነዚህ መሆናቸው፡ በመሲሐዊ ባህርያቶቹ አስተዋወቀ።

182 ሴቲቱም ያለችው አንድ አይነት እንደሆነ ተመልከቱ። "ጌታየ፡ ነብዪ እንደሆንክ አያለሁ። ለብዙ አመታት ነብዪ አልነበረንም። ብዙ ቸርቾች፣ ብዙ ትርምስ እና ብዙ የሃይማኖት ተቋማት ልዩነቶች ነበሩን፡ ነብዪ ግን ለብዙ ዓመታት አልነበረንም። መሲሑ ሲመጣ ግን፡ እሱ የሚታወቅበት ይሄ ነው።"

183 "ከአንቺ ጋር የምናገረው፡ እኔ እርሱ ነኝ።" ምንም የሚያጠራጥር ነገር የለውም፡ "እኔ እሱ ነኝ።" ይሄ እሱን ያስተዋውቃል።

184 የደም ችግር የነበራት ሴት፡ ቃል የሆነውን እሱን አውቃዋለች። እንዴት? እምነቷ ሲነካው ባደረገው ነገር ነው። ዘወር ብሎ፡ "የነካኝ ማን ነው? አላቸው" የሆነ ነገር እንደተፈጠረ አውቋል። ይህም ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን ገልጿል።

185 አመነች እና፡ እንዴ ብቻ "ልብሱን መንካት ከቻልኩ፡ እድናለሁ፡" አለች።

186 እንደነካችው፡ ዞር ብሎ፡ "አሁን የነካኝ ማን ነው? አለ" ሁሉም ካዱ። መሲሐዊ ባህሪው ግን...

187 አሜን! ጉባኤ ሆይ፡ እንዳያችሁት ተሰፋ አደርጋለሁ። እስኪ ሰናጠቃልለው፡ አድምጡኝ።

188 ይሄው እሷ ነካችው። ምናልባት፡ እሱን የሚዳስሱ፡ ብዙ መቶዎች ነበሩ። ጴጥሮስ፡ "ይሄው፡ ሰው ሁሉ እየዳሰሰህ ነው" በማለት፡ እስኪገስጸው ድረስ።

189 እሱ ግን፡ "አዎን፡ አንድ ሰው ግን ለየት አርጎ ነክቶኛል" አለ። አያችሁ? የእምነት አነካክ፡ ይሄን ያህል ይለያል። እንዲህ አለ፦ "አንድ ሰው ነክቶኛል። ለየት ያለ አነካክ ነው። ድካም ተሰምቶኛል። አሁን፡ ጉልበት ከእኔ ወጥቷል። ኃይል ከእኔ ተወሰዷል።" በማለት ቆም ብሏል።

190 አሁን በሌላ ቋንቋ፡ ደቀ መዛሙርቱ እንኳን ሳይቀሩ፡ "ስትናገር—— እነጋገርህ ግድ የለሽ ሰው መሰልክ፡ ብለውታል። ለምን፡ ሰው ሁሉ እያጋፈህ'ኮ ነው፡ አሉ።"

191 ተመልከቱት :መታወቂያው አሁን እዩት። ወደ ኋላው ዞር አለና፡ በህዝቡ መካከል ፈለገ። መንጥሮ አወጣት። ከዚያ ወዲያ መሸሸግ አልቻለችም። ችግሯን ገለጾ ነገራት፡ "እምነትሽ አድኖሻል፡" አላት።

192 ከዚህ የተነሳ፡ ዕብራውያን 4:12ን፡ "ቃሉ የልብ ስሜት እና፡ ውስጣዊ ሐሳብ መርማሪ መሆኑን፡" በዚህ፡ አውቃዋለች። ባህርያቶቹ ሁሉ "የእግዚአብሄር ቃል ሰጋ ሆኖ በእኛ ዘንድ ማደሩን" ያስታውቃል። አሜን።

193 ዛሬ ምሽት እሱን የሚያስተዋውቀው ተመሳሳይ እንደሆነ አስባለሁ፡ ዛሬ ምሽት አብሮን ያለውን፡ የተነሣው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ትናንትናና፡ ዛሬ እስከ ዘለአለም ድረስ ያው ነው። ዕብራውያን 13:8 እውነት እንደሆነ ሁሉ፡ ያኔ እንዳደረገ፡ አሁንም በተመሳሳይ መንገድ፡ ዛሬም የራሱ ባህርይ፡ እሱን ይገልጸዋል።

194 ከትንሳኤው በኋላ፡ ቄልዮጳን እና ሌሎቹን ተመልከቷቸው። እንጀራውን የቆረሰበት መንገድ እርሱን አስተዋወቀበት፡ ከመስቀሉ በፊት በቆረሰበት መንገድ ቆረሰው። እነሱም... ይህም ባህሪውን አስታወቀ፡ ምክንያቱ የቆረሰበት መንገድ ይህ ነውና።

195 አሁንስ ዛሬ ምሽት እዚህ ቢሆን፡ እራሱን በምን መልኩ ያስተዋውቃል? ልክ ትናንትና እንዳደረገ፡ ዛሬ እና ለዘለአለም፡ ያው ስለሆነ። ይህ መታወቂያው ነው። "እሱ አሁንም... " ዕብራውያን 4፡ አራት-... 14 እና 15፡ "በድካማችን ስሜት ሊነካ የሚችል ሊቀ ካህናችን ነው፡" ይለዋል። አሁን ሊቀ ካህናችን ነው። ከትንሳኤው በኋላ፣ ከሞቱ በኋላ፣ ከቀብሩ በኋላ፣ ከትንሳኤው በኋላ፣ ከዕርገቱ በኋላም፣ አሜን፡ አሁንም ትናንትናና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘለአለም ድረስ ያው ነው፡ በድካማችን ስሜት ሊነካ የሚችል ሊቀ ካህን ነው። አሜን። አሁንም፡ ለሚያምን ወንድ እና ሴት ሁሉ፡ ሊቀ ካህን ነው። እሱ ትናንትናና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለም ድረስ፡ ሊቀ ካህናችን ነው።

196 ህያው ነው። ታምናላችሁ? [ጉባኤው፡ "አሜን" አለ።—እርታዒ።] ያኔ በምድር እንደ ነበረ አሁንም ያው እንደሆነ የራሱ ባህርይ ዘወትር ያስረዳል። ዛሬ ማታም፡ በመንፈስ ቅዱስ አምሳል፡ አሁንም ድረስ እዚህ አለ። ህያው ነው። እስከ አሁን ድረስ ህያው ከሆነ፡ ሁሌ እንደሚያደርጉት፡ ባህርያቶቹም ይከተሉታል።

197 ዛሬ ማታ፡ ምስጋናዬ፡ ብዙ ነው፡ "እግዚአብሄር፡ ብዙ ጊዜ እና በልዩ ልዩ ጉዳና ለአባቶቻችን በነብያት ተናግሮ፡ በዚህ በመጨረሻ ዘመን ግን በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ተናገረን።"

198 ማይ፡ ይሄን ያህል እንደተናገርኩ አላስተዋልኩም። እንዲህ መሆኑ ረሳሁት። ይቅርታ አርጉልኝ። በቃ... አቆማለሁ።

እንጸልይ።

199 የሰማይ አባት፣ ታላቅ መሐሪ አምላክ! ጌታ ሆይ፡ ምናልባት—ብዙ... ተናግሬ ይሆናል። አምላክ ሆይ፡ ተናግሬ ከሆነም፡ ይቅር እንድትለኝ እጸልያለሁ። ነገር ግን፡ ጌታ ሆይ፡ ላልኩት ይቅርታ መጠየቅ አልችልም። አንተ በቃልህ እዚህ የተናገርከውን ብቻ ተናግሬአለሁና።

200 አሁን ካንተ አንድ ወይም ሁለት ቃል ብቻ፣ ጌታ ሆይ፣ ምናልባት እዚህ ያሉት ሁሉም ሰዎች ዛሬ ማታ ያዩታል። የታመሙ ሰዎች፡ ዛሬም አንተ ታላቁ ሊቀ ካህናችን መሆንህን ሲገባቸው ይድናሉ። ጌታ ሆይ፣ በሚቀጥሉት ጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ፣ ይህ መልእክት በእውነት እንደገና ህያው እንድታደርገው እጸልያለሁ። ዛሬ፡ እኔ በቃል የተናገርኩት የአንተ ባህርይ፡ አንተን በእኛ መካከል እንድትታወቅ ያድርግ፡ ይህም አንተ ትናንትናና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘለአለም ድረስ ያው መሆንህ ነው፡ በኢየሱስ ስም እንጸልያለን። አሜን።

201 አሁን ለአፍታ ያህል። እንደው—ትንሽ ዘግይቻለሁና፣ እኛም፣ ለአሰራ አምስት፣ ሃያ ደቂቃ ያህል ትንሽ የጸሎት መስመር እንዲኖረን በደንብ ትታገሡኛላችሁ? ፍቃደኞች ከሆናችሁ፡ እጆቻችሁን ወደ ላይ ከፍ አርጉና፡ እንዲህ በሉ፡ "ሁላችንም… " በጣም ጥሩ፡ አመሠግናለሁ—አመሠግናለሁ። ዘጠኝ-ተኩል እልካችኋለሁ ብየ ቃል ገብቻለሁ። አሁን እየደረሰ ነው፡ ከሀያ ሆኗል። ብቻ አስር ደቂቃ ከሰጣችሁኝ፡ ቶሎ ቶሎ እላለሁ።

202 እስኪ እንየው፡ ዛሬ የተሰጠ የጸሎት ካርድ ምንድነው? [አንድ ወንድም "ከኦ፡" ነው አለ።—አርታዒ] ኦ? ባለፈው ማታ፡ ከምን ነበር የጀመርነው፡ ከአንድ ነው፡ ከአንድ? ["አንድ ይመስለኛል።"] አዎን፡ አህ-ሀህ።

203 ከዚያ በኋላ፡ ባለፈው ማታ፡ እንደው እኛ… መንፈስ ቅዱስን… ዛሬ እያዳመጥኩት ነበር፡ እና የተባለው እየደጋገምኩት ነበር። አንዳንዶቹ የፍሬንች ሰዎች ናቸው፡ እኔ፡ ማድረግ ያለብኝ ብቸኛው ነገር… መንፈስ ቅዱስን መጠባበቅ፡ ከዚያ በኋላ ማየት ነው።

204 አያችሁ፡ አንዳንዴ ራእይ ሰታዩ፡ አዙራችሁ መተርጎም ያስፈልገዋል። በቃል ተተርጉሟል። ለምሳሌ በራእይ—በግ ልታዩ—ትችላላችሁ፡ ትርጉሙ ግን የበግ ጠጉር ሊሆን ይችላል። አያችሁ፡ የጽሑፍ ትርጉምም መያዝ ያስፈልጋችኋል፡ አያችሁ፡ ራዕዩን መልሳችሁ በጽሑፍ ትተረጉሙታላችሁ።

205 እና ትናንት ማታ፡ እነዚያ የፍሬንች ሰዎች—በትክክል መጥራት ስላልቻልኩ፡ በፊደል እየጠራሁ እንደነበርኩ አስተዋልኩኝ።

206 በአፍሪካ ውስጥ በሆተንቶት እና እምነት አልባዎች፡ የመሳሰሉ ዙርያ፡ ሰዎቻቸው በትክክል መጠራት አለበት፡ ማን መሆናቸው ይነገራቸዋል፡ በገዛ ቋንቋቸው በትክክል መነገር አለበት። እነሱ፡ ልክ ሰትጠራቸው፡ ምን መሆኑን ወድያው ይረዱታል። አያችሁ፡እሱ ግን፡ ቋንቋዎቹን ሁሉ ያውቃል። እሱ ዘለአለማዊ አምላክ ነው።

207 እስኪ ዛሬ፡ ኦ ላይ፡ ከሰባ-አምስት፡ እስከ መቶ ድረስ፡ እንጀምረው። ኦ ነው፡ ያለው ኦ ነው አይደል? እኔ… [አንድ ወንድም "አዎን። ኦ፡" አለ።] ኦ፣ ኦ። አዎን። በጣም ጥሩ። የጸሎት ካርድ ቁጥር ሰባ አምስት የያዘ ማን ነው፡ እስኪ እንየው? ኦ ላይ፡ የጸሎት ካርድ ኦ፡ ሰባ-አምስት፡ የያዘ ሰው፡ እጁ ወደላይ ያንሣ። ኦዎች። በጣም ጥሩ። ና **ወደዚህ** ጠጋ በል። ሰባ-አምስት፣ ሰማንያ፣ ሰማንያ-አምስት፣ ዘጠና፣ ዘጠና-አምስት፣ መቶ፡ ከቻላችሁ **ወደዚህ** ኑ። በጣም ጥሩ፡ ጊዜ ስለሌለን፡ በፍጥነት፡ እዚህ ጋር፡ ተሰለፉ። ታደርጉታላችሁ ብየ ብቻ አምናለሁ።

208 የጸሎት ካርዳችሁን ተመልከቱት። አጠገባችሁ የተቀመጠ ሰው የጸሎት ካርዳቸውን ተመለከቱ። ምናልባት… አቅማቸው የደከመ ሰዎች ካሉ፡ ወደዚህ ወደ ጸሎት ሰልፍ እንዲመጡ አግዟቸው። የያዙት ኦ ከሆነ፡ ኦ እንደ፡ ሰባ-…

209 ሰባ-ኣምስት እስከ መቶ፡ ከቻላችሁ፡ **እዚህ** ጋር ተሰለፉ። ባልኮኒው ላይ ያላችሁ፡ ሌላም ላይ ያላችሁ፡ የትም ብትሆኑ፡ ወደዚህ ወደታች ውረዱ፣ ከቻላችሁ፡ ጊዜ ለመቆጠብ፡ በተቻለ ፍጥነት ወደ ሰልፉ ውረዱ።

210 አሁን ሌሎቻችሁ እዚህ ላላችሁ፡ የጸሎት ካርድ የሌላችሁ፡ እጃችሁን አውጥታችሁ፦ "ወንድም ብራንሃም፡ እኔ የጸሎት ካርድ አልደረሰኝም፡ ነገር ግን እምናለሁ" ትላላችሁ? እጆቻችሁን አንሱ።

211 አሁን አስታውሱ፣ ስለ ሊቀ ካህናቱ እናገራችኋለሁና። "እርሱ በድካማችን ስሜት ሊነካ የሚችል ሊቀ ካህናት ነው።" እሱ **ያሕዌ-ይርኤ** ነው፡ "መስዋዕትን አቅራቢ ጌታ።" እሱ **ያሕዌ-ራፋ** ነው፡ "ደዌሽን ሁሉ የሚፈውስ ጌታ።" ይሄን ታምናላችሁ? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።] እሱ **ያሕዌ-ንሲ** ነው። **ከለላ፡ ጋሻ፡ ሰላማችን**፡ አሁንም ነው። እሺ፡ እነዚህ የእግዚአብሄር የቤዛነት ስሞች ሁሉ ለእየሱስ መስጠታቸውን ስንቶቻችሁ ታምናላችሁ? ["አሜን።"] በትክክል፡ እንዲህ—እንዲህ ከሆነ... ለምን፡ ፈጽመው የማይነጣጠሉ ናቸውና፡ ስለዚህም እነዚህን ሁሉ ሊኖሩት ይገባል። ስለዚህ እስከ አሁን ድረስ ያሕዌ-ይርኤ ከሆነ፡ ያሕዌ-ራፋም ነው። እሱ ያሕዌ-ይርኤ ከሆነ... **ያሕዌ-ይርኤ**፣ "የመዳንን መስዋዕት የሚያዘጋጅ ጌታ ነው፡" እንዲሁም ደግሞ **ያሕዌ-ራፋ** "ደዌዎቻችን ሁሉ ይፈውሳል።" አሜን። ፈውስ በእግዚአብሄር ብቻ ነው መምጣት የሚችለው።

212 በጣም ጥሩ፡ ሰዎቹ እየተሰለፍ ሳሉ፡ እነማን መሆናቸውን እና ምን መሆናቸውን ለማየት ጊዜ የለኝም። አሁን ግን፡ እኔ እንደማላውቃችሁ የምታውቁ ሁላችሁ፡ እጆቻችሁን ወደ ላይ አንሡና፡ እንዲህ በሉ፦ "እግዚአብሄር ያስፈልገኛል። ወንድም ብራንሃም፡ አንተ እኔን አታውቀኝም፡ እግዚአብሄር ግን የሚያስፈልገኝ ሰው ነኝ። ስለዚህ እጄን ከፍ አደርጋለሁ በሉ።"

213 ለጥቂት ደቂቃ መታገስ ከቻላችሁ፡ ጸጥ በሉ፡ ጸልዩ፡ ጥንቃቄ አድርጉ። "ጸጥ በሉ፡" ስላችሁ፡ እንዲህ ማለቴ አይደለም፡... ጌታ ሲሰራ፡ ለጌታ ክብር መስጠት ትችላላችሁ፡ አምልኮ ነውና። እኔ ማለት የፈለግኩት፡ "ወዲያ ወዲህ መሯሯጥ፡ መነሣት፡ ንቀት ነው። አያችሁ? መንፈስ ቅዱስ ቶሎ የሚደናቀፍ ነው፡ ቶሎ ይደናቀፋል። አያችሁ? በመሰል ነገሮች፡ ቶሎ ከእኔ ይለያል፡ አያችሁ፡ እንደገና፡ መታገል ይኖርብኛል። ከሰማችሁኝ ግን!

214 መጀመርያ የገባልኝ ቃል አስታወሳችሁ? "ሰዎች እንዲያምኑህህ አድርጋቸው፡ ከዚያ በኋላ ትሑት ሁን፡ ጸሎትህን መቋቋም የሚችል ነገር አይኖርም።" ይሄን ታስታውሳላችሁ? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።] ትክክል። ይህም... እስከ አሁን ድረስ ሲወድቅ አላየሁትም፡ ደግሞም አይወድቅም። አምላክ ነውና።

215 አሁን የቻልነውን ያህል፡ የሰዎችን ቁጥር ለማዳረስ፡ ወደ ጸሎት መስመሩ እንጣደፋለን። የጸሎት ካርድ ወሰዳችሁ ያልተጠራችሁ ሰዎች፡ ካርዶቻችሁን ያዙ፡ እናገኛችኋለን። በጣም ጥሩ።

216 እናንተም፡ የጸሎት ካርድ ያልወሰዳችሁ አስታውሱ። ወይም፡ እዚህ ያላችሁ፡ የጸሎት ካርድ ይኑራችሁ አይኑራችሁ፡ እሱ አሁንም እንደ ዕብራውያን 4ኛው ምዕራፍ እንደሆነ እመኑ። "እርሱ በድካማችን ስሜት ሊነካ የሚችል ሊቀ ካህናት ነው።" እሱ አሁንም... አያችሁ ያሕዌ አሁንም በሶዶም ዘመን እንዳደረገ፡ እራሱን በሕዝቡ መካከል ከወከለ። በጣም ጥሩ።

217 መልካም፡ ጋሼ። አሁን እንጸልይ፡ አሁን፡ በእውነት ትሑታን ሁኑ። ይህን አትርሱ፡ አንዲት ቃል ከእግዚአብሄር ማለት ማንም ከሚለው በላይ ነው።

አሁን፡ ይህ እዚህ ያለውን ሰውየ፡ እኔ—አላውቀውም። እሱም ይመስለኛል… ለኔ እንግዳ ሰው ነህ፡ አይደል፡ ጋሼ? [ወንድማችን "አዎን፡" አለ።—እርታዒ።] እንግዳ ነህ። አንድ ቀን ሁለታችንም በእግዚአብሄር ፊት እንደምንቆም፡ ይህን አንድ ነገር እናውቃለን፤ እንደ ሰው፡ በዚያ መገኘታችን አይቀርም። ስንገናኝ መጀመርያ ቀናችን ነው።

218 አሁን ወደዚህ የመጣኸው፡ ታመህ ከሆንክ፡ እኔ አላውቅም፡ ሌላም ነገር ሊሆን ይችላል፡ አየህ። ነገር ግን እጄን—በአንተ ላይ ጭኜ፡ "ክብር ለጌታ ይሁን! ደህና ሆነህ፡ ተመለስ፡" ብልህ። ችግር የለውም። ልታምነኝ ትችላለህ። ግን አንተ ምን እንደሆንክ እሱ ቢነግርህስ? አሁን፡ አየህ፡ ይሄ ሌላ ነገር ነው፡ በዚህ የእሱ ባህርይ ለይተህ ታውቃለህ። አየህ፡ የእኔ ባህርይ ሊሆን አይችልም። ሰው ነኝና፡ እኔ ስለ'ሱ እንዳች ላውቅ አልችልም። አስቀድሜም "እኔ አላውቅህም፡" ብየዋለሁ። እሱም አያውቀኝም። ታድያ ይሄስ ምን ይጠቅማል? የኢየሱስ ክርስቶስ ባህርይ፡ ትናንትናና፡ ዛሬ እስከ ዘለአለም ድረስ ያው እንደሆነ ያስተዋውቃል። ሰውየውን ስለማላውቀው፡ እኔ እንዳልሆንኩ፡ ልሆንም እንደማልችል በማወቅ ነው። **ይሄው** ቃሉ በፊቴ ነው፡ እጄን አነሣለሁ። አያችሁ? እኔ አላውቀውም። እሱም እኔን አያውቀኝም። የኢየሱስ ክርስቶስ ባህርይ ግን…

219 ኢየሱስ ክርስቶስ እዚህ ቆሞ ቢሆን፡ እና እሱ፡ ከታመመ፡ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ፈውሰኝ፡" ቢለው፡ ኢየሱስ ምን ይለው ነበር? "ቀድሞም ፈውሼኃለሁ።" ልክ ነው? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—እርታዒ።]

220 "ስለመተላለፋችን ቆሰለ፡ በመገረፉ ቁስል ተፈውሰናል።" ለእኛ የሚገባ ቤዛነት ሁሉ በቀራንዮ ተፈጽሟል። ከዚያ ጀምሮ፡ ያለቀውን ስራ ለማመን፡ እምነት ብቻ ይጠይቃል። ልክ ነው? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—እርታዒ።] በጣም ጥሩ።

221 አሁን፡ ኢየሱስ አሁን ህያው ከሆነና፡ እኔ ስለ ቃሉ ከተናገርኩ… ይሄውላችሁ፡ ወደ እምነቱ እና ትህትና መመለስ፡ ቃሉን ማመን ብቻ ነው። እኔን ያገኘባት በዚያች ምሽት፡ እንዲህ አለኝ፡ "የልቦናቸው ምስጢር እስከማወቅ ድረስ ትደርሳለህ። የመጀመርያው የእጅ ምልክት ካላመኑ፡ ይሄኛው ማምመን አለባቸው።" አያችሁ? "ይሄን ካላረጉ ግን፡ ምድር በደም ትረገማለች።"

222 ልክ በሙሴ ዘመን እንደሆነ። እንዲህ አለ፡ "እነዚህ ሁለት ምልክቶች ካላመኑ፡ እንግዲያውስ ደም በምድር አፍስስ አለው፡" አያችሁ፡ "በምድር ላይ ደም አፍስስ፡ ደምም ይሆናል።"

223 እስኪ አሁን ችግርህ ምን እንደሆነ፡ ማየት ከቻልኩ ለመፈተሽ፡ እንድታምን እና እንድትረካ ያግዝሃል፡ አያግዝህም? [ወንድማችን "በትክክል፡" አለ።—እርታዒ።] እኔ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የምነግረው ሰው ባህርይ፡ ወሳኝ እንደሆነ ታውቃላችሁ።

224 ይህ ሰው፡ ወደ ኋላው ተመልሼ፡ ሳየው። ጥላ አጥሎበት አየዋለሁ። ይህ ሰው ሊፈውስ የሚችል መድኃኒት አይገኝም። በሞት አፋፍ ላይ ነው። ትክክል። ቀዶ ጥገና አድርጓል፡ የፕሮስቴት ቀደ ጥገናው ነው። ካንሰር ነው፡ ካንሰሩ መላ ሰውነትህ ላይ ተሰራጭቷል። ይህ ትክክል ከሆነ፡ እጅህን ወደ ላይ አንሣ። ከእግዚአብሄር በቀር የሚፈውሰው የለም። [ወንድማችን ሃሌሉያ! ሃሌሉያ! ሃሌሉያ!" አለ፡—እርታዒ።] አንድ ነገር፡ ግን፡ ልበልህ፡ ስማኝ ጋሼ።

ይህ ዲያብሎስ ከዶክተሮች ሰንጢ ተሰውሮ ሊሆን ይችላል፡ ከእግዚአብሄር ግን አያመልጥም። ታምናለህ? ታምነዋለህ ወይ? [“ኦህ! ኦህ!”] ስለዚህ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እጸልያለሁ፡ ነገርየው ይልቀቀው፡ በህይወት ይኑር። ምንም አይደል፡ መድከም ብቻ ነው። በጣም ጥሩ።

225 እኔ እና አንቺ አንተዋወቅም፡ አንድ ሰውየ እና አንዲት ሴትዮ መገጣጠማቸው ብቻ ነን። አሁን፡ እንደ ሰው፡ እኔ አላውቅሽም። አንቺም፡ እንደ ሰው፡ ስሜን ከማየት፡ ወይም ፎቶየን፡ ወይም መሰል ነገሬን ከማየት በዘለለ፡ እኔን አታውቂኝም። ሁለታችንም አንተዋወቅም። ባህርያችን ይህ ነው። ሁለታችንም ባህርያችን አንተዋወቅም። የክርስቶስ ባህርይ ግን፡ ቃል ነው፡ ቃሉም ለዚህ ዘመን ቃል ተገብቷል። ስለሱ ሰናገር ሰምተሻል። እንግዲያውስ የራሱ ባህርይ አሁን እሱን እዚህ ይገልጠዋል። እኔ አንቺን አላውቅሽም። ተረድተሸኛል። የኛ—ጉባኤውም ይሄን ተረድታችኋል? [ጉባኤው “አሜን፡” አለ።—አርታዒ።] አያችሁ? እኔ—ሰው ነኝ። ወንድማችሁ ብቻ ነኝ።

226 በውኃው ጉድጓድ አጠገብ እንደነብረች ሴት፡ ችግርሽ ብናገር፡ ወይም ይህ ችግር አለብሽ ብልሽ፡ ወይም የምትፈልጊው ነገር፣ ወይም ለምን ወደዚህ መጣሽ። የዚያ ሁሉ ዳኛ እግዚአብሄር ይሁን። በአነሚያ ሰቃይ ነሽ ያለሽው። ትክክል ነው፡ አይደለም′ዴ? [እህታችን “አዎን፡” አለች።—አርታዒ።]

227 እኔ—በተደጋጋሚ እመክራለሁ፡ ግምት እንደገመትኩ የሚያስብ አለ። አልገመትኩም። አይደለም። በየተወሰነ ደቂቃ፡ ከሆነ ሰው፡ ያንን ስሜት ይመጣብኛል። የምታስቡት ነገር አሁን መደበቅ አትችሉም። ሁለት ክፉኛ ተጠራጣሪዎች፡ እዚህ ተቀምጠው እንዳሉ፡ አውቄአለሁ። አያችሁ? አሁን ሰሞቻችሁ፡ ጭምር፡ መጥራት እችላለሁ፡ እግዚአብሄር ይችላል፡ ስለዚህ የምታስቡትን አቁሙት። ላሳያችሁ።

228 ወደዚህ እዩ፡ እመቤት። እኔን እዩኝ። ምን እንደነገርሽ እኔ አላውቅም፡ እሱ ማን እንደሆነ ግን—አውቀዋለሁ። ባህርዪው የሚታወቅበትም በዚህ ነው። አዎን፡ የአነሚያ እክል ነው፡ የደም፡ ውሃ ነው።

229 አሁን፡ ሌላ ደግሞ፡ ሌላ አለ። አየሽ ግምት ነው ብለው ለሚያስቡ። አንቺ እየጸለይሽለት ያለ ልጅሽ፡ እዚሁ አለ። [እህቲቱ “አሜን፡” አለች።—አርታዒ።] ትክክል ነው። [“አዎን።”]፡ ቶንሲል፡ አደኖይድስ፡ ጉሮሮው፡ ላይ አለ። ለቀዶ ጥገና ቀጠሮ ላይ ነው። ይህ ትክክል ነው? [“አዎን።”] ያንን መሀረብ ወሰደሽ፡ በላዩ ላይ አድርጊበት፡ እና እምነት ይኑርሽ። [“እሺ።”] አትጠራጥሪ። ቀዶ ጥገና አያደርግም። በሙሉ ልብሽ ብቻ እመኚ።

230 እንዴት ነህ? ጉዳይህ፡ እጅግ የፈራህላት ሴት አለች፡ እዚህ አለች። የልደት ምልክቷ ወደ ካንሰር እንዳይቀየር ፈርተሃል። አህ-ሀህ፣ አህ-ሀህ። በል አሁን፡ እያመንክ ሂድ፡ እንደፈራኸው አይሆንም። ብቻ በሙሉ ልብህ እምነህ፡ ሂድ። ባህርያቶቹ፡ የእሱ ናቸው፡ የኔ አይደሉም!

231 አሁንስ እመናችሁ? [ጉባኤው “አሜን፡” አለ።—አርታዒ።] ሰው ሁሉ እንዲያምን የሚያደርግ ነው። [“አሜን!”]

232 አሁንም፡ እኔ አንቺን አላውቅሽም። እኔም ለአንቺ እንግዳ ነኝ። እግዚአብሄር ግን ያውቅሻል። ታምኛለሽ… ? እኔ እንደማላውቅሽ ታውቂያለሽ፡ አንቺም እንደማታውቂኝ ታውቂያለሽ፣ ስለዚህ አሁን የሚናገርሽ መንፈስ የእኔ መንፈስ

እንዳልሆነ ታምኚአለሽ? ምክንያቱ፡ እኔ፡ እንደ ሰው፡ አንቺን አላውቅሽም። ተሰፋ የተሰጠበት ቃል ባህርይ ግን ከሁለት-አፍ ከተሳለው ይልቅ ስለታም ቃል ነው፣ የልብን አሳብ እና ስሜት ይመረምራል።

233 እጅግ አሞሻል። የሴቶች ችግር ነበረብሽ፡ ማሕጸንሽ ውስጥ ነው፡ ማሕጸንሽ ውስጥ ካንሰር አለ። ሄደሽ አንዳንድ ህክምና አድርገሻል፡ የራዲየም ህክምና ነው፡ ከዚያም ያተረፍሽው ብቸኛው ነገር ወደ መላ ሰውነትሽ መሰራጨቱ ነው። እና እግዚአብሄር አንቺን ካልፈወሰሽ—ሟች ነሽ። አዎን ትክክል ነው። እሱ እንደሚፈውስሽ አሁን ታምኛለሽ? [እህታችን "አዎን፡" አለች።—አርታዒ።] ከህኪም የተሰወረውን ሰይጣን የሰማይ አምላክ ይገስጽ። ["ኦህ!"] ከራዲየም ተደብቆ ሊሆን ይችላል፣ ከመንፈስ ቅዱስ ግን አይችልም። አሁን፣ ሂጂ፣ አመኚዉ፣ እህት። እመኚ እንጂ፡ ፈጽመሽ አትጠራጠሪ።

234 አምላክ ያንን የአስም በሽታ እንደሚፈውስህ፡ እና እንደሚያድንህ ታምናለህ? [ወንድም "አዎን፡" አለ።—አርታዒ።] አምነሃል? እንግዲያውስ "ጌታ ሆይ፡ አመሰግንሃለሁ፡ አሰሜ ለቆኛል።" እያልክ፡ በደስታ፡ መንገድህን ሂድ።

235 እንዴት ነሽ? ጭንቀት አለብሽ። ለብዙ ጊዜ በጭንቀት ቆይተሻል። በዚያም፡ ሆድሽ—እንዲያምሽ፡ በሆድሽ ውስጥ ፔፕቲክ አልሰር እንዲነሳ ምክንያት ሆኗል። እና አንቺ የምትፈልጊው... እራት መብላት ትፈልጊአለሽ? አርጊ የምልሽን ታደርጊአለሽ? በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ሂጂና፡ ብዪ።

236 በሙሉ ልብሽ አምነሻል? [እህታችን "አዎን አምናለሁ፡" አለች።—አርታዒ።] ኃያል ወጣት እመቤት ነሽ፡ ታስታውቂአለሽ። እኔ ባርያው እንደሆኑኩ ታምኚአለሽ? ["አሜን።"] የእሱ ባህርይ አሁን እዚህ ሊኖር እንደሚችል ታምኛለሽ፡ ለ... ለቃሉ፡ ለራሱ፡ እና ለዘመኑ ተሰፋ ቃል፡ "እኔ የማደርጋቸውን ስራዎች እናንተም ታደርጋላችሁ"? ["አሜን።"] እኔ ማዳን አልችልም። አሰቀድሞ ፈጽሞታል፡ ባህርይ ግን እሱ ይገልጸዋል፡ ችግርሽም እርሱ ይናገራል። የእመቤቶች ችግር አለብሽ፡ የሴቶች ችግር። [አዎን፡ ጌታዩ።"] እግዚ አብሄር አሁን እንደፈወሰው ታምኛለሽ? ["አዎን። አሜን።"] መንገድሽን ቀጥይ፡ ከእንግዲህ አያሰቸግርሽም።

237 እኔ ባርያው እንደሆንኩ ታምኛለሽ? [እህታችን "አዎን፡ ጌታየ፡" አለች።—አርታዒ።] እግዚአብሄር የአንቺን ችግር ከነገረኝ፡ ይህ የኢየሱስ ክርስቶስ ባህርይ መሆኑን ታምኛለሽ? ጀርባሽ ላይ ነው። አሁን የለም። ሂጂ፡ በሙሉ ልብሽ እመኚ። እመኚ።

238 ነይ፡ እመቤት። አንቺም የሆድ ችግር አለብሽ። በሙሉ ልብሽ እመኚና፡ ሄደሽ እራትሽን ተመገቢ። እርሽው። ኢየሱስ ክርስቶስ ፈውሶሻል።

239 ና። ችግርህ ደምህ ነው። የስኳር ህመምተኛ ነህ። እግዚአብሄር ከዚህ ህመም ነጻ እንደሚያደርግህ እና እንደሚፈውስህ ታምናለህ? መንገድህን ቀጥልና፡ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ተመስገን፡" ፈውሰኸኛል፡ በለው። በሙሉ ልብህ አምነህ፡ ሂድ።

240 ነይ። የወገብ ህመም፡ እግዚአብሄር ወገብሽን እንደሚፈውስሽ እና ነጻ እንደሚያደርግሽ ታምኛለሽ? በደስታ፡ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ አመሰግንሃለሁ፡" እያልሽ፡ መንገድሽን ቀጥይ።

241 አንቺም የወገብ ችግር አለብሽ። እንዲህ እያልሽ ብቻ፡ ሂጂበት፡ በሙሉ ልብሽ እመኚ። "ጌታ ሆይ፡ ተፈውሻለሁ። አመሰግንሃለሁ።"

242 አንተም ተመሳሳይ የወገብ ህመም ነው። ስለዚያስ ምን ታውቃለህ? አሁን በሙሉ ልብህ እመን፡ እና መንገድህን ሄደህ ተፈወስ። ኢየሱስ ክርስቶስ እንደፈወሰህ እመን። "የማይቻል እንደሌለ፡ አንተ ማመን ከቻልክ።" በጣም ጥሩ።

243 እስኪ ምንም ካልተናገርኩሽስ፡ ዝም ብየ አንቺን አልፌ እጆቼን በሷ ላይ ብጭን፡ እንደምትፈወስ ታምኛለሽ? ችግሩን አይተውታል። እንደምትፈወስ ታምኛለሽ? ወዲህ ነይ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ይህን ዲያብሎስ እገስጻለሁ። የእግዚአብሄር ኃይል ህጻኒቱን ይፈውስ። አሜን። አትጠራጠሪ፡ በፍጹም አትጠራጥሪ፡ ትድናለች። ከልብሽ እመኚ።

244 እግዚአብሄር አንቺን ካልፈወሰሽ፡ በአርቲራይትስ ምክንያት አንድ ቀን በክራንች ትሄጃለሽ። ነገር ግን እግዚአብሄር አርተራይትሽን እንደፈወሰሽ እምነሻል? በይ፡ "ጌታ ሆይ፡ አመሰግንሃለሁ። እምንሃለሁ፡ አንተ ፈውስኸኛል፡" እያልሽ ሂጂ። በጣም ጥሩ።

245 አሁን ነይ። በርግጥ ዕድሜሽ ነው። በትክክል ጭንቀት አለብሽ። በጣም ሲመሽ፡ ትጨነቂያለሽ። ስራ ስትሰሪ ወዘተ፡ የእውነት ጭንቀታም ነሽ። አሁን አምነሻል? እንግዲያውስ ከአሁን በኋላ አያስቸግርሽም። "ጌታ ሆይ፡ አመሰግንሃለሁ፡" እያልሽ፡ መንገድሽ ሂጂ።

246 ወዲህ ና፡ ጋሼ። እግዚአብሄር የልብ ህመም እንደሚፈውስ ታምናለህ? ልብህ ጤነኛ እንደሚያደርግ? [ወንድማችን "አዎን፡" አለ።—አርታዒ።] እንዲህ እያልክ ብቻ፡ ተንቀሳቀስ፡ "ጌታ ሆይ፡ አመሰግንሃለሁ። ከልቤ አምናለሁ።"

247 እግዚአብሄር ቲቢንም፡ ጭምር፡ መፈወስ ይችላል። ይሄን፡ ከልብህ ታምናለህ፡ ጋሼ? [ወንድማችን "አዎን፡" አለ።—አርታዒ።] በጣም ጥሩ። "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ አመሰግንሃለሁ፡" እያልክ፡ጉዞህን ቀጥል።

248 እናንተ እዚያ ያላችሁስ፡ ታምናላችሁ? ጉባኤውስ? አንዳንዶቻችሁ በጉባኤው ውስጥ አሁን አምናችኋል።

249 እዚህ ጋር የተቀመጠው ሰውየ፡ ብሮንካይት አለበት፡ እግዚ አብሄር ብሮንካይት በሽታን እንደሚፈውስ ታምናለህ? በጣም ጥሩ፡ እንግዲያውስ፡ የለመንከውን ማግኘት ትችላለህ። አሜን።

250 እዚያ ጋር ከሱ በስተጀርባ የተቀመጥከው፡ ኃይለኛ ደም ግፊት አለብህ። ደም ግፊትህን እግዚአብሄር እንደሚፈውስ ታምናለህ? ለቆሀል፡ ጋሼ። በዘመኔ አይቼው አላውቅም፡ አላውቀውም።

251 እርሶ፡ ጋሼ፡ ጡንቻዎቾ ውስጥ ያሉትን መኮማተር፡ የጡንቻ መኮማተር ጭንቀት፡ እግዚአብሄር ደህና እንድሚያደርግ ታምናለህ? ታምናለህ? ከአመንክ እጅህን ወደ ላይ አድርግ። በጣም ጥሩ።

252 እዚያ ጋር የተቀመጠችው ሚስትህ፡ በሳይነስ ህመም ትሰቃያለች። አንቺንም እንደለቀቀሽ፡ ታምኛለሽ፡ እህት?

253 ከእና ጀርባ ተቀምጣ ያለችው ያቺ ሴት፡ የኒውራይትስ ህመምተና ናት። እግዚአብሄር የኒውራይትስ ህመምሽ እንደሚፈውስ ታምኛለሽ፡ እመቤት?

254 እዚህ አንዲት ሴት አለች፡ ቀይ ካፖርት የለበሰች ሴት፡ አለች። እዚያ ተቀምጣለች። እሷም፡ የሳይነስ ችግር አለባት። የሳይነስ ህመምሽ እንደሚፈውስሽ እግዚ አብሄርን ታምኛለሽ? ካመንሽ፡ እጅሽን ከፍ አርጊ።

255 ዛሬ ማታ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ባህርይ በእኛ ዘንድ መኖሩ የሚያምን ማንም ሰው እዚህ ካለ፣ እጅህን አውጣና፡ "እኔ እምናለሁ፡" በል። [ጉባኤው ሁሉ ተደሰቶ እንዲህ አለ፦ "እኔ እምናለሁ!—አርታዒ።]

256 እዚህ ያላችሁ ሁላችሁ፡ እሱን እንደፈዋሻችሁ የተቀበላችሁት፡ በእግሮቻችሁ ለመቆም ተነሱና፡ "እኔ እምናለሁ፡" በሉ። ከየወንበሮቻችሁ፡ ተነሡ። ቁሙ፡ ምንም ይሁን። ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትናና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘለአለም ድረስ ያው ነው። በጌታ በአምላክ ስም፡ ለአንተ አሳልፌ ሰጠሁ።

**እግዚአብሔር በገዛ ባህርያቶቹ እራሱን ያስተዋውቃል** AMH64-0320

(God Identifying Himself By His Characteristics)

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ በመጋቢት 20፡ 1964፡ እርብ ማታ፡ በልዊዝያና፡ ዴንሃም ስፕሪንግስ ትምህርት ቤት በዴንሃም ስፕሪንግስ፡ U.S.A.፡ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይስ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግስ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2022 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org

# የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈለጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org